# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 076 ኅዳር 16 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም

- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

# የአምራች ኢንዱስትሪዎች የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግሮች ተፈትተዋል ባይባልም መሻሻል አሳይቷል

## - 144ሺህ አርሶ አደሮች ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር ፈጥረዋል

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡-የኢንዱስትሪና የግብርና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በፈጠሩት ቅንጅት የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የጥሬ ዕቃ ችግሮቻቸው ተፈትተዋል ባይባልም ማቃለል መቻሉን ተገለጸ፡፡ 144ሺህ አርሶ አደሮች ከኢንዱስትሪዎች ጋር የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ትስስር መፍጠራቸው ተጠቁሟል፡፡

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴንና የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሁለቱ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በፈጠሩት ቅንጅት በጋራ ማቀዳቸውንና አፈጻጸሙን በየጊዜው እየገመገሙ በመሄዳቸው፤የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግሮቻቸው ተፈትተዋል ባይባልም ከዓመት ዓመት መሻሻል እየታየ ነው፡፡አሁንም የአግሮ የኢንዱስትሪዎችን የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ ለማሟላት ብዙ ሥራ ይጠይቃል ብለዋል፡፡

የኢንዱስትሪውን የጥሬ ዕቃ ፍላጎት ለማሟላት ኢንዱስትሪው ከግብርናው የሚፈልገውን የጥሬ ዕቃ ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ማወቅ ያስፈልጋል ያሉት የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን፤ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በጋራ አቅደውና አፈጻፀማቸውን በጋራ መገምገማቸው የአምራች ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ ችግር እየተቃለለ መሄዱን ተናግረዋል፡፡

ከ2014ዓ.ም በፊት የመኮሮኒና የዱቄት ፋብሪካዎች በጥሬ ዕቃነት ይጠቀሙት የነበረው ስንዴ በዕርዳታ ወይም ገበያውን ለማረጋጋት ተብሎ ከውጭ ይገባ የነበረው እንደነበር አስታውሰው፤ ከአምና ጀምሮ እነዚህ ፋብሪካዎች የሚጠቀሙት በሀገር ውስጥ የተመረተውን ስንዴ ነው፡፡ የአቅርቦትም ችግር አለብን ብለው እሮሮ


የአምራች.. ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡ አሸናፊ ጉደታ

# "የሰላም ስምምነቱን ማደናቀፍ የትግራይ ሕዝብ በችግሮች ውስጥ ይኑር ብሎ መፍረድ ነው"

አቶ መስፍን ደሳለኝ
የትዴፓ ምክትል ሊቀመንበር

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ እንዳይሆን የተለያዩ ሰበባ ሰበቦችን እየፈለጉ ስምምነቱን ወደኋላ ለመመለስ የሚሞክሩ ኃይሎች የትግራይ ሕዝብ በጦርነት አዙሪት ውስጥ ሆኖ በተደራራቢ ችግሮች ውስጥ ኑሮውን እንዲገፋ መፍረድ ነው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር አቶ መስፍን ደሳለኝ ገለጹ፡፡


የሰላም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# በአላማጣ በጦርነቱ ምክንያት ተቋርጠው የነበሩ አገልግሎቶች 75 ከመቶ ተመልሰዋል

## - በሚቀጥለው ሳምንት ሁሉም አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ሥራ ይጀምራሉ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አላማጣ፡- በግጭት ውስጥ በቆየችው አላማጣ ተቋርጠው የነበሩ አገልግሎቶች 75 ከመቶ መመለሳቸውን እና በሚቀጥለው ሳምንት ሁሉም አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ወደሥራ እንደሚገቡ የአላማጣ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የአላማጣ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ኃይሉ አበራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ የአላማጣ ከተማ ከግጭት በወጣች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰባ አምስት በመቶ የሚሆነው አገልግሎት ወደ ነበረበት ተመልሷል።

በተለይ የውሃ አገልግሎት በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው፣ የ2Gና የ3G የኢንተርኔት አገልግሎት ጀምሯል። በቀጣይ በጦርነት የተበጣጠሱ ፋይበሮችን በመጠገን ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት ይጀምራል ብለዋል።

እንደ ከንቲባው ገለጻ፤ በከተማዋ የመብራት አገልግሎትም ወደ ነበረበት ተመልሷል።

በከተማዋ ያሉ የንግድ ድርጅቶች ተከፍተው ለኅብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውንም ገልጸዋል።

ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ለማስገባት ከተማ አስተዳደሩ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ነው ያሉት ከንቲባው፤ በሚቀጥለው ሳምንት ሁሉም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ወደ መደበኛ ሥራቸው ይመለሳሉ ብለዋል።


በአላማጣ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ፡ ሳሙኤል ተስፋዬ



አቶ ኃይሉ አበራ

# በዲፕሎማሲ መስክ የተከናወኑ ተግባራት ለሀገር ሉዓላዊነትና ለሰላም ስምምነቱ አስተዋጽኦ አበርክተዋል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ጥቅሟን ለማስከበር ከኃያላን ጋር ጭምር በመተናነቅ በዲፕሎማሲ መስክ ያከናወነቻቸው ተግባራት ለሀገር ሉዓላዊነትና ክብር እንዲሁም ለሰላም ስምምነቱ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክተር ከፍተኛ አማካሪ አቶ ሙክታር መሐመድ አስታወቁ፡፡

አቶ ሙክታር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ የዲፕሎማሲ ሥራ በየትኛውም ዓለም እጅግ ውስብስብ ከመሆኑ በተጨማሪ አብዛኛውን ጊዜ


በዲፕሎማሲ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከ400 ሚሊዮን ዶላር በላይ የብድር ስምምነት አጸደቀ

- የሚዲያ ተቋማቱን እንደገና ለማቋቋም የወጡ ረቂቅ አዋጆችንም አጽድቋል


ገጽ 3

# ምክር ቤቱ ለወረዳ የመጅሊስ አመራሮች ሹመት ሰጠ

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- የተጀመረውን ሀገራዊ ለውጥ በሁሉም ዘርፍ ከዳር ለማድረስ እንዲቻል የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት በወረዳ ደረጃ የመጅሊስ አመራር ሹመት ሰጠ።አዳዲሶቹን የወረዳ መጅሊስ አመራሮቹንም ቃለ-መሐላ በማስፈጸም ሥራ አስጀምሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሱልጣን አማን በመድረኩ እንደተናገሩት፣ በመዲናዋ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ወረዳዎች የመጅሊስ ቢሮዎች እንደ አዲስ ተዋቅረዋል።በሁሉም ወረዳዎች የራሱን የወረዳ መጅሊስ ቢሮዎች አደራጅቷል።በተደራጁት ሁሉም ወረዳዎች ስር ባለው የመጅሊስ መዋቅር እንደ አዲስ አዳዲስ የወረዳ መጅሊስ አመራሮቹን ሹመት በመስጠት ሥራ አስጀምሯል፡፡

አዲስ የተሾሙትን አመራሮችም በእለቱ ሕዝቡን ለማገልገልና እንደ ሀገር የተጀመረውን ሀገራዊ ለውጥ በሁሉም ዘርፍ ከዳር ለማድረስ ምክር ቤቱ ሥራ አስጀምሯል፡፡

አዲስ ሹመት ለተቀበሉት የወረዳ መጅሊስ አመራሮችም የተሾማችሁት ሰፊውን ሕዝብ ለማገልገል ነው።በመሐከል እንደመገኘታችሁ ለወቀሳም፤ ለሙገሳም የቀረባችሁ መሆኑን አውቃችሁ እራሳችሁን አዘጋጅታችሁ በጠንካራ መንፈስ ልትሠሩ ይገባል ሲሉ ፕሬዚዳንት ሼህ ሱልጣን ጠይቀዋል፡፡

እንደሀገር የመጣውን ለውጥ ተከትሎ መጅሊሱ በአዲስ ቁመና ላይ ነው ያለው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ የእምነቱን መርሆዎች ተከትለው ለሀገር ግንባታና ሰላም ሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሚጠበቅበትን ሥራ ያለ እረፍት እንዲሠራ ይጠበቃል ብለዋል።

የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ሼህ ፈቱሁዲን ሐጂ ዘይኑ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያውያን በነበረባቸው ተቋም የመመሥረት ትግል ምክንያት መጅሊሱ ተገቢውን የአገልግሎት ሥራ ሳይሠራ መቆየቱን አውስተው፤ በቀጣይ እንደ ሀገርና ተቋም የሚጠበቅበትን ተደራራቢ ሥራ በስኬት ለመወጣት ሁላችንም በትብብር ልንሠራ ይገባል ብለዋል።

በመድረኩ ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ እንደተናገሩት፣ በተቋሙ የተዋቀረው አዲሱ መዋቅር በቀጣይ ጠንክሮ ሊሠራ ይገባዋል ብለዋል።

አዲስ አበባ ለሀገራችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ዋነኛ መነሻ ነች ያሉት ፕሬዚዳንቱ ሼህ ሐጂ ኢብራሂም፤ በእምነቱ በኩል ከተማዋ ለመላው ኢትዮጵያ እንደ መሪ የምትቆጠር ናት፣ አዲስ ሹመት የተቀበላችሁት ይህንን ተረድታችሁ በጥንካሬ እንድትሠሩ ነው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ፕሬዚዳንቱ ሼህ ሐጂ ኢብራሂም አክለውም፣ በአዲስ አበባ ከተማ መጅሊስ በኩል በክፍለ ከተማና ወረዳዎች የተደራጁ ሲሆን መዋቅሩን ወደ መስጅዶችም በማውረድ እንዲቀጥል መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ገለጻ፣ የወረዳ አመራሮች ሰፊው ማኅበረሰብ ጋር የቀረቡ ናቸው።ኅብረተሰቡን በተገቢው መልኩ በቅንነት፣ በተረጋጋና በታማኝነት ለማገልገል ልትሠሩ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

## ዓለም አቀፍ የሥራ ፈጣሪነት ሳምንት በአዲስ አበባ ሲካሄድ ነው

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ የሥራ ፈጣሪነት ሳምንት ከኅዳር 20 ጀምሮ ለተከታታይ ስድስት ቀናት "ሚሊዮን ፈተናዎች...ሚሊዮን ዕድሎች" በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በአገራችን የሥራ ፈጣነትን /ኢንተርፕረነርሺፕን/ ባህል ለማድረግ እየሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በዓለም ለ15ኛ በኢትዮጵያ ደግሞ ለዘጠነኛ ጊዜ በሚካሄደው ዓለም አቀፍ የሥራ ፈጣሪነት ሁነት ላይ ከ200 በላይ አገራት የሚሳተፉ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን አስታውቀዋል።



አቶ ንጉሡ ጥላሁን

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለፈው አንድ ዓመት ከአመራሮች ጀምሮ ለተጠሪ ተቋማት እና በተዋረድ አደረጃጀቶች እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ለሚገኙ አመራሮች የአቅም ግንባታ ሥራ መስጠቱን ገልጸዋል።

ዘንድሮ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በአዋጅ ሲቋቋም የሥራ ፈጣሪነት ሥራንም በተቀናጀና በተደራጀ ሁኔታ ይመራ ዘንድ የቀድሞውን ኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ደረጃውን ወደ ተቋምነት አሳድጎ እንዲመራው ተወስኖ ወደ ሥራ መገባቱን አስታውሰዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለሥራ ፈጣሪነት የሚያበቃ አስተሳሰብ መቅረፅና በሀገራችን የሥራ ፈጣሪነት ሥነ ምህዳር ግንባታን ለማስፋፋት በማቀድ እየሠራ መሆኑን የጠቆሙ ሲሆን የዘንድሮው የኢንተርፕረነርሽፕ ሳምንት በኢንተርፕረነርሺፕ፣ በትምህርት፣ በሥነ-ምህዳር፣ በፖሊሲና፣ አካታችነት ጉዳዮች ያተኮረ ነው ብለዋል።

የዓለም የሥራ ፈጣሪነት ሳምንት የሚኒስቴር መሥሪያቤቶችን፣ ዩኒቨርሲቲዎችን፤ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኮሌጆችን፤ ዘርፉ እንዲስፋፋ የሚደግፉ የልማት ተራድኦ ድርጅቶችን፤ እንዲሁም ፈር ቀዳጅ የሆኑ የግል ድርጅቶችን ያቀፈ ነው ብለዋል።

የክብረ በዓሉ ዋና ተግባር ለስኬታማ ሥራ ፈጣሪዎች ዕውቅና በመስጠት፤ ችግሮችን በመፍታት በማኅበረሰቦቻቸው፣ በአካባቢያቸው፤ አልፎም በቀጠናቸው ላይ የሚያመጡትን በጎ ለውጥ መዘከር መሆኑን ጠቁመዋል።

"ሥራ ፈጣሪዎች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ለብዙዎች የማይታዩትን መልካም አጋጣሚዎችና አደጋዎች አስቀድመው የሚያዩ፣ ባለራዕይዎች ናቸው። በወድቆ መነሳት ዝንባሌአቸው ለሌሎች አርአያ ናቸው" ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በሀገራችን የሥራ ፈጣሪነት መስፋፋት የማክሮ ኢኮኖሚ አንዱ ስብራት የሆነውን የሥራ አጥነት ችግርን ከመፍታት በዘለለ የወጣቶቻችንን አስተሳሰብ፤ ባህሪና፤ ስነምግባር ለማነፅ በመሳሪያነት የሚያገለግል መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም የበለፀጉት ሀገራት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዕውቀት ኢኮኖሚያቸው ሞተር እንደሆኑት ሁሉ የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎችና የቴክኒክና የሙያ ስልጠና ኮሌጆች በሥራ ፈጣሪነትና ኢኖቬሽን ታንፀው ምርታማ ሃሳቦች መፈልፈያና ማበልጸጊያ እንዲሆኑ በዕቅድ እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

በየሥራ ፈጣሪነት ሳምንቱ በሥራ ፈጣሪዎች ፣ፖሊሲ አውጭዎችና አስፈጻሚዎች መካከል ምቹ ሥነምሕዳር በመፍጠር ዙሪያ ምክክር ይደረጋል፤ በፐብሊክ ሥራ ፈጠራ የተሠሩ ሥራዎች ይገመገማሉ፤ የፈጠራ ሀሳብ ውድድሮች፤ የልምድ ልውውጦች፤ የቴክኖሎጂ ኤግዚቢሽን፤ የዕውቅና መድረኮች ይደረጋሉ ብለዋል፡፡

የመንግሥት፤ የግል፤ መንግሥታዊ የልሆኑ ተቋማት ሥራ ፈጣሪነትንና ኢኖቬሽንን ለማበረታትና ለማስፋፋት የየራሳቸውን መርሐግብር በማዘጋጀት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ፤ የልማት አጋሮቻችን የሥራ ፈጣሪነትና ኢኖቬሽንን ባህል ለማድረግ የተወሰደውን እርምጃ በመከተል ሁለንተናዊ ድጋፋቸውን እንዲያደርጉልም ጥሪ አቅርበዋል።

## በአዲስ አበባ የምግብ ሸቀጦች የዋጋ ንረትን ለመግታት ያለመ የጥናት ውጤት ይፋ ሆነ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**



የምክክር መድረኩ ሲካሄድ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በመዲናዋ እየተስዋለ ያለውን መሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎች ዋጋ ንረት ለመግታት የሚያስችል የጥናት ውጤት ይፋ አደረገ፡፡

ቢሮው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና የማዕከላዊ ስታስቲክስ አገልግሎት ባለሙያዎችን በማሳተፍ "መሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎች አቅርቦትና ፍላጎት ሁኔታ ላይ" ያስጠናው ጥናት ላይ በትናንትናው እለት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር አድርጓል፡፡

በጥናቱ ለዋጋ ንረት ተገቢ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል በመዲናዋ የሚዘወተሩ መሠረታዊ የምግብ ፍጆታዎች፣ የአቅርቦታቸው ሁኔታ፣የአቅርቦትና የፍላጎት ክፍተት እንዲሁም ምግቦቹ ከየትኛው አካባቢ በስፋት ወደ መዲናው እንዲገቡ የመለየት ሥራ ተሠርቷል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ እንደገለጹት፣ አዲስ አበባ ከተማ የሀገሪቱ ዋና ከተማ፣የአፍሪካ መዲና እና የዓለም አቀፍ ተቋማት መገኛ በመሆኗ በማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች በአራቱም አቅጣጫዎች ወደ መዲናዋ የሚፈስ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡

በዚህ ምክንያት የምግብ አቅርቦትና ፍላጎት ባለመመጣጠኑ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በመዲናዋ ከፍተኛ የምግብ ፍጆታ ዋጋ ንረት ተስተውሏል።የከተማ መስተዳደሩም በዋጋ ንረቱ ምክንያት የተከሰተውን የኑሮ ውድነት ለመግታት ጊዜያዊና ዘላቂ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን እያበጀ ይገኛል፡፡

ዳሩ ግን ለመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ዋጋ ንረት ትልቁ መንስኤ የአቅርቦትና የፍላጎት አለመመጣጠን መሆኑን የተናገሩት አቶ አደም፤ በተመሳሳይ መልኩ የንግድ ሥርዓቱ ክትትልና ቁጥጥር መላላት፣ ምርትን የመደበቅ እና በግብይት ሰንሰለቱ የበርካታ ተዋናዮች ጣልቃገብነት እና የጸጥታ ችግር ለዋጋ ንረቱ ሌላኛው ግብዓት መሆናቸውን በጥናቱ መለየታቸውን አስገንዝበዋል፡፡

ንግድ ቢሮው ዋጋ ንረቱን ለመቀልበስ በዩንዬኖችና በሸማቾች አማካኝነት ለሸማቹ ማኅበረሰብ የሚያቀርባቸውን ምርቶች አጠናክሮ እንዲቀጥልና አቅርቦትን ለመጨመር ከአምራቾች ጋር ምርትን ወደ ማምረት የመግባት እቅድ እንዳለውም አቶ አደም ጠቁመዋል፡፡

የጥናቱ ቡድን መሪ አቶ እንዳለ ተገኝ በበኩላቸው፣ በመዲናዋ የሚዘወተሩ የምግብ ምርቶች 23 መሆናቸውን በጥናቱ መለየታቸውን ገልጸው፤ እነዚህም ጥራጥሬ፣አትክልትና ፍራፍሬ ፣ የእንስሳት ተዋጽዖ እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ተብሎ እንደሚመደቡ አብራርተዋል፡፡

በጥናቱ መሠረት፣ በአሁኑ ጊዜ የመዲናዋ ሕዝብ ቁጥር 5 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሲሆን ከሕዝቡ ጠቅላላ ወጪ 52 በመቶው የምግብ ፍጆታ ወጪ ነው። ከእነዚህ ወጪዎች ጤፍ 57 ነጥብ 7 በመቶ በመያዝ ቀዳሚ ደረጃን ይይዛል። ስንዴ፣ቀይ ሽንኩርት እና ድንች በቅደም ተከተል ከ2ኛ እስከ 4ኛ ደረጃን ይይዛሉ። በርበሬ፣ ወተት፣ዘይት፣ሥጋ፣ እንቁላል እና ስኳርም በመዲናዋ በጣም ተፈላጊ የምግብ ሸቀጦች ናቸው፡፡

ከምግቦቹ ምንጭ አንጻር የመዲናው ሕዝብ በብዛት የሚጠቀመው ምርቶች፤ በጤፍ አደዓ፣ በስንዴ አቡሴራ፣ በቀይ ሽንኩርት ሸዋሮቢት፣ በዳልጋ ከብት ሐረር፣በምግብ ዘይት ማሌዥያ፣ በስኳር ሕንድ ቀዳሚ ደረጃ ላይ መሆናቸውን የገለጹት አቶ እንዳለ፤ ለዋጋ ንረቱ እንደ ምክንያቶች የተጠቀሱትን ችግሮች በመግታት ያሉትን ምርቶች በአግባቡ ካልተጠቀምን እንዲሁም ምርትና ምርታማነት ካልተጨመረ አሁን የተስተዋለው እጥረት በእጥፍ እንደሚጨምር በጥናቱ መለየቱን አስታውቀዋል።



# ከአራት ሺህ በላይ ተቋማት የክፍያ ሥርዓታቸውን በሲኔት ቴክኖሎጂ አዘመኑ

**- ቴክኖሎጂውን ከቴሌብር ጋር በማጣመር የክፍያ ሥርዓት ተዘርግቷል**

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ሲኔት (CNET) ሶፍት ዌር ቴክኖሎጂን በመጠቀም 4 ሺህ 200 ተቋማት አገልግሎታቸውን ማዘመን መቻላቸውን ኢትዮ ቴሌኮም ገለጸ፡፡ ኢትዮ ቴሌኮም ከሲኔት ሶፍትዌር ቴክኖሎጂ ጋር በፈጠሩት ቅንጅት የሲኔት ቴክኖሎጂንና ቴሌብርን በማስተሳሰር የአገልግሎት እና የግብይት ክፍያዎችን በቴሌብር ለመፈጸም የሚያስችል አሠራር ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩንም በትናንትናው ዕለት አሳውቋል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ታምሩ በትናንትናው ዕለት ስምምነቱን ሲያከናውኑ በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ሲኔት ሶፍት ዌር ቴክኖሎጂን በመጠቀም 4 ሺህ 200 ተቋማት አገልግሎታቸውን አዘምነዋል፤ ይህም ዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ትልቅ ድጋፍ ያደረገ ነው።

ዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ በኢትዮ ቴሌኮም ጥረት ብቻ የሚሳካ አይደለም ያሉት ሥራ አስፈፃሚዋ፤ ሲኔትን መሰል ቴክኖሎጂዎች የማኅበረሰቡን ሕይወት የሚያቀሉ በመሆናቸው አስፈላጊ ናቸው ብለዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም እና ሲኔት ሶፍትዌር ቴክኖሎጂ የሲኔት ሶፍትዌር ተጠቃሚ አጋሮች ደንበኞቻቸው የአገልግሎትና የግብይት ክፍያቸውን በቴሌብር አማካኝነት ተግባራዊ ያደረጉት አሠራር ቴሌብርንና ሲኔት ሶፍትዌርን በማስተሳሰር የሲኔት ሶፍትዌር ተጠቃሚ አጋሮች ደንበኞቻቸው ግብይት ሲያከናውኑ ቴሌብርን ተጠቅመው የአገልግሎት ክፍያቸውን እንዲፈጽሙ እንደሚያስችላቸው አብራርተዋል፡፡

ቴክኖሎጂው የሲኔት ሶፍትዌርን በመጠቀም አገልግሎት የሚሰጡ ሆስፒታሎች፣ ፋርማሲዎች፣ ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና ሌሎች መሰል ተቋማት በቀላሉ የተለያዩ የአገልግሎት እና የግብይት ክፍያዎቻቸውን እንዲያከናወኑ ይረዳቸዋል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ደንበኞች የአገልግሎት ወይም ግብይት ክፍያዎችን ለመፈጸም የአገልግሎት ሰጪውን ተቋም ወይም ድርጅት ኪው አር ኮድ (QR code) በማንሳት እንዲሁም በቅድሚያ ክፍያቸውን በቴሌ ብር እንደሚከፍሉ በማሳወቅ በተንቀሳቃሽ ስልካቸው በሚደርሳቸው የክፍያ የሚስጥር ቁጥር ክፍያቸውን በቴሌብር መተግበሪያ ወይም አጭር ቁጥር (USSD) ሲፈጽሙ ከ127 የክፍያ ማረጋገጫ አጭር የጽሑፍ መልዕክት በሚደርሳቸው መሠረት መክፈል እንደሚችሉ ተነግሯል፡፡

በተዛማጅ ኢትዮ ቴሌኮም ቴሌብር መላን ለግለሰብ ደንበኞች፣ ነጋዴዎች እንዲሁም ወኪሎች የአነስተኛ ብድር አገልግሎት በቴሌ ብር አካውንታቸው አማካኝነት የሚያገኙበትን አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆኑን የጠቀሱት ሥራ አስፈፃሚዋ፤ የቴሌብር ደንበኞች በአካውንታቸው ላይ ያላቸው ቀሪ የሂሳብ መጠን በቂ ባልሆነበት ጊዜ ከወለድ ነጻ ወይም የተለያየ የወለድ የሚጠቀሙት ቴሌ ብር እንደኪሴ እንዲሁም ቴሌ ብር ሳንዱቅ የመሳሰሉ የቁጠባ ዓይነቶችን የሚጠቀሙበት ፋይናንስ ለሁሉም በሚል መርሕ በማቅረብ የፋይናንስ አካታችነትን በማረጋገጥ ላይ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም በቴሌ ብር አገልግሎት እስከ አሁን ድረስ 25 ነጥብ 85 ሚሊዮን ደንበኞችን ማፍራት መቻሉንም ወይዘሪት ፍሬሕይወት አብራርተዋል፡፡

# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከ400 ሚሊዮን ዶላር በላይ የብድር ስምምነት አጸደቀ

**- የሚዲያ ተቋማቱን እንደገና ለማቋቋም የወጡ ረቂቅ አዋጆችንም አጽድቋል**

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት በ2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 6ኛ መደበኛ ስብሰባው ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘውን የ400 ሚሊዮን ዶላርና ከጣሊያን መንግሥት የተገኘ የ10 ሚሊዮን ዩሮ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ አጸደቀ፡፡ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትንና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬትን እንደገና ለማቋቋም የወጡ ረቂቅ አዋጆችንም አጽድቋል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት በ2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 6ኛ መደበኛ ስብሰባው ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘውን የ400 ሚሊዮን ዶላር የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 1281/2015ና ከጣሊያን መንግሥት የተገኘ የ10 ሚሊዮን ዩሮ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ 1280/2015 አድርጎ በአብላጫ ድምፅ አጽድቋል፡፡

የፕላን በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ደሳለኝ ወዳጄ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጆችን ለምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት ከምክር ቤቱ ለተነሳላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ሰብሳቢው በኢትዮጵያ መንግሥትና በጣሊያን መንግሥት መካከል የጤናውን ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ለሚከናወነው ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ነው፡፡ ብድሩ ካሁን በፊት በገንዘብ ላልተደገፉ የጤና ዘርፍ እቅዶች ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን ረጅም የችሮታ ጊዜና ዜሮ ነጥብ አምስት አነስተኛ የወለድ መጠን ያለው ነው፡፡ ይህም ከአገሪቱ የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር የተጣጣሙና ጫናው ያልበዛ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ደሳለኝ ለምክር ቤቱ በሰጡት ማብራሪያ፤ መንግሥት ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተደረገው የ400 ሚሊዮን ዶላር የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ የሥርዓተ ምግብ ማስፈጸሚያ ፕሮግራም የሚለውን ነው፡፡ ገንዘቡ የምግብ ዋስትና ችግር አለባቸው ተብለው የተለዩ 181 ወረዳዎችን ያቀፈ ሲሆን አንድ ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎችን በቀጥታና 2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ በዋናነት የምግብ ዋስትና ችግርን ለመቅረፍ፣ ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል፣ የገበያ ትስስርን ለመፍጠርና የኢኮኖሚ እድገቱን ለማፋጠን ያለመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የምክር ቤት አባላትም የብድር ስምምነቱን በበጎ መልኩ ተቀብለው ብድሩ ለታለመለት ዓላማ እንዲውልና ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጣ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ መሠራት አለበት ሲሉ አሳስበዋል፡፡

ምክር ቤቱ በትናንት ውሎው የሕግ፤ ፍትሕና ዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትንና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት እንደገና ለማቋቋም ያቀረበው ረቂቅ አዋጅ በሰፊው ተወያይቶ በአብላጫ ድምጽ አጽድቀዋል፡፡

የሕግ፤ ፍትሕና ዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እፀገነት መንግሥቱ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን እንደገና ለማቋቋም የወጣውን ረቂቅ አዋጅን ሲያብራሩ፤ ኮርፖሬሽኑ ከአገሪቱ ለውጥ ጋር አብሮ እንዲሄድ በማድረግ በሀገሪቱ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ቁልፍ ሚና ለመጫወት እንዲችል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በአዲስ መልክ የፀደቀው አዋጅ ተቋሙ ሀገራዊ ተልዕኮውን በተሟላ ቁመና ለመወጣትና እየገጠሙት ያሉ መዋቅራዊ ችግሮቹን ለመሻገር እንደሚያስችለው አብራርተዋል።

ምክር ቤቱ የቀረበለትን ረቂቅ ከመረመረ በኋላ በ44 ተቃውሞ በ24 ድምፀ ተዓቅቦ አዋጅ ቁጥር 1278/2015 ሆኖ እንዲጸድቅ በአብላጫ ጸድቋል፡፡ የአዲሱ አዋጅ መጽደቅን ተከትሎ የኢትዮጵያን ብዝኃነት ያማከለ እና በዓለም አቀፍ ዐውድ ብሔራዊ ጥቅሟን ሊያስጠብቅ በሚችል ሙያዊ ቁመና ላይ ሆኖ ተልዕኮውን እንዲወጣም የምክር ቤት አባላት አሳስበዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትን እንደገና ለማቋቋም የቀረበለትን አዋጅ 1279/2015 በአራት ድምፀ ተአቅቦ በአብላጫ ድምፅ አጽድቋል። በተጨማሪም የምክር ቤቱን 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 5ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ መርምሮ አጽድቋል፡፡

# የኢኮኖሚክ ዞን መቋቋሙ ኢትዮጵያ በቀጠናው ያላትን የንግድ ተሳትፎ ወደላቀ ደረጃ ያሸጋግራል

**ገመቹ ከድር**



አዲስ አበባ ፡- ስፔሻል የኢኮኖሚ ዞን ፖሊሲን ወደተግባር በመቀየር ምቹ ገበያ ትስስር በመፍጠር ኢትዮጵያ በቀጠናው ያላትን ንግድ ተሳትፎ ወደላቀ ደረጃ እንደሚያሸጋግር የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ ኮሚሽኑ ስፔሻል የኢኮኖሚክ ዞን ለማቋቋም በረቂቅ አዋጁ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይቷል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ነሜ በውይይቱ ላይ እንደገለጹት ፤ የአዋጁ መሻሻል ስፔሻል ኢኮኖሚክ ዞን በማቋቋም የሀገሪቱን የማምረቻ ኢንዱስትሪ ዘርፎችን ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚደረገውን ጥረት ያግዛል ፡፡

ኢንዱስትሪ ፓርኮች በሥራ ዕድል ፈጠራ ፣የውጪ ንግድን በማሳደግ ፣ የእውቀትና ክህሎት ሽግግር በማሳለጥ ኢትዮጵያን የአፍሪካ ኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ የተቀረጸውን የኢንዱስትሪ ፖሊሲ እውን ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥር ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ጉዞ መልካም ቢሆንም ዘርፉ በሚፈለገው ደረጃ ማይክሮ ኢኮኖሚ ለውጥ ለማምጣት እና የኢኮኖሚ ትስስር መፍጠር ላይ የሚስተዋሉ ውስንነቶችን ለመፍታት ስፔሻል ኢኮኖሚክ ዞን አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ፣የውጪ ንግድ ለማበረታት የሥራ ዕድል ለመፍጠር ፣ የኢኮኖሚ መስኮችን ለማስፋት ፣ የተቀናጀ የምርት ሂደት ለማረጋገጥ የስፔሻል ኢኮኖሚክ ዞን መቋቋም ሚና ትልቅ ነው ሲሉም ተናግረዋል ፡፡

ረቂቅ ሕጉ የተስተዋሉ ክፍተቶችን በመሙላት ኢትዮጵያ ተወዳዳሪ በሆነችባቸው መስኮች ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ የሚያደርግ ነው ያሉት ኮሚሽነሯ በአፍሪካ የነጻ ንግድ ስምምነት የሚጠበቅባትን ግዴታ እንድትወጣ በማድረግ ንግድ ቀጠናውን ለማስፋት የምታደርገውን ጥረት እንደሚያፋጥን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ሕግ አማካሪ ዶክተር ሀብታሙ ስማቸው ለውይይቱ መነሻ የሚሆን ጽሑፍ በአቀረቡበት ወቅት ስፔሻል ኢኮኖሚክ ዞን ረቂቅ አዋጁ ከፖሊሲው የተቀዳ በመሆኑ ሕግ ሆኖ እንዲወጣ የባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት መደረጉ አስፈላጊ ነው፡፡ አዋጁ ጸድቆ ወደ ሥራ የሚገባ ከሆነ በተለያዩ ሀገሪቱ ኮሪደሮች በርከት ያሉ ስፔሻል ኢኮኖሚ ዞን እንዲኖሩ ያደርጋልም ብለዋል ፡፡

የሕግ ማዕቀፉ በስፔሻል ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የግሉ ሴክተር ተሳትፎ እንዲጨምር በማድረግ የወጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት መጨመር ፣ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የንግድ ትስስሮች ውስጥ የሚያስገባ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በአፍሪካ ንግድ ቀጣና ውስጥ ኢትዮጵያ ድርሻዋን እንድታገኝ ስፔሻል ኢኮኖሚክ ዞን በማቋቋም ማምረትና መነገድ ግዴታ ነው ያሉት አማካሪው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ንግድ ሰንሰለት ውስጥ ሊያስገቡ የሚችሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሊኖራት ይገባል ብለዋል፡፡

የሕግ ማዕቀፉ በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ውስጥ ትልልቅ ባለሀብቶች ኢንቨስት በማድረግ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ንግድ ቀጠና ውስጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ መጓተቶች እንዳይኖሩ አብዛኞቹ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች የሚኖራቸውን ስልጣን በውክልና ለሚያስተዳድረው አካል የሚሰጡበትን አግባብ የሚፈጥር በመሆኑ ረቂቅ አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ የሁሉም ድጋፍ ያስፈልጋል ብለዋል ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ግርማ ሰይፉ ስፔሻል ኢኮኖሚክ ዞን መቋቋም አስፈላጊና ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

ዱባይ አሁን ለአለችበት ደረጃ የደረሰችው እንደነዚህ ዓይነቱን ስፔሻል ኢኮኖሚክ ዞን በመፍቀድ ባለሀብቶችን በመሳቧ ነው፡፡ ሌሎችም አንድ መቶ አርባ የሚሆኑ ሀገራት ስፔሻል ኢኮኖሚ ዞን አቋቁመው መለወጣቸውን ጠቅሰው በሀገራችንም ዞኑ ተግባራዊ ተደርጎ በውጤቱ የሚለካ ይሆናል ሲሉ አስፈላጊነቱን ገልጸዋል፡፡

ዜና

# የዲያስፖራ አደረጃጀት ጥምረት አባላት ለሰላም ስምምነቱ ስኬታማነት መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት እንደሚደግፉ አስታወቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡ በመላው ዓለም የሚገኙ 21 የዲያስፖራ አደረጃጀት ጥምረት አባላት ለሰላም ስምምነቱ ስኬታማነት መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት እንደሚደግፉ አስታወቁ፡፡

የጥምረቱ አባላት ይህን የገለጹት ከአንድ ሺ በላይ ለሚሆኑ የሀገራትና የዓለም አቀፍ ተቋማት መሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ሚዲያዎች በላኩት የአቋም መግለጫ መሆኑን ኢ.ቢ.ሲ. ዘግቧል።

በአሜሪካ፣ አውሮፓና ካናዳ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አደረጃጀቶችን በመወከል መግለጫውን ያወጡት የጥምረቱ አባላት በደቡብ አፍሪካና በኬንያ በፌደራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል ለተደረሰው የሰላም ስምምነት ያላቸውን ድጋፍ ገልጸዋል፡፡

ስምምነቱ ዕውን እንዲሆን « የአፍሪካን ችግር በአፍሪካ መፍታት ይቻላል» የሚለውን መርሕ በማራመድ የአፍሪካ ኅብረት ላበረከተው አስተዋፅዖና ለስምምነቱ ተግባራዊነት ለሚያሳየው ቁርጠኝነት አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

ሆኖም በውጭ ያሉ አንዳንድ አካላት፣ የአንድ አንድ ሀገራት ፓርላማ አባላት፣ ሚዲያዎችና ተቋማት የሰላም ስምምነቱን መንፈስ የሚያውክና ገንቢ ያልሆነ አስተያየት




በመስጠት በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ሕዝቦች በግጭት አዙሪት ውስጥ እንዲቆዩ የሚያደርጉት አፍራሽ እንቅስቃሴ እንዳሳዘናቸው ገልጸዋል።

በአንጻሩ የተገኘውን የሰላም ዕድል በመጠቀም የኢትዮጵያ መንግሥት ሰብዓዊ ድጋፍና መሠረታዊ አገልግሎቶችን በፍጥነት ለማቅረብ እያከናወናቸው ስላሉ ተግባራት አድናቆታቸውን ገልጸው፣ ሕወሐትም በበኩሉ ትጥቅ የመፍታት ቁርጠኝነቱን ሊያሳይ ይገባል ብለዋል።

ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በተለይም የአሜሪካና የአውሮፓ ኅብረት የሰለም ሂደቱን በመደገፍ ከኢትዮጵያ ጋር ላላቸው ዘላቂ ግንኙነትና የጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት እንዲሰጡ ጠይቀዋል፡፡

የሰላም ሂደቱን ለማጨናገፍ እየተንቀሳቀሱ ያሉ አካላትም ከአጥፊ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ አሳስበዋል፡፡

የሕወሓት አመራሮችም የሰላም ስምምነቱን ለማስፈጸም ያላቸውን ቁርጠኝነት እንዲያሳዩ የጠየቁ ሲሆን በመላው ዓለም የሚገኙ የዲያስፖራ አባላትም የሰላም ሂደቱን ለመደገፍ የጀመሩትን ሥራ አጠናክረው እንዲቀጥሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ከዲያስፖራ አገልግሎት የተገኘው መረጃ እንዳመላከተው ዲያስፖራው በግጭት ምክንያት የደረሰውን ጉዳት ለመጠገን የሚያስፈልገውን ድጋፍ ለማሰባሰብ እንዲሠራና በሁለቱም ወገን የተጎዱ የኅብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ ለማቋቋም እንዲንቀሳቀስ ጠይቀዋል።

## በአሳማጣ በጦርነቱ ምክንያት...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ወደ ሥራ ያልገቡ የንግድ ተቋማት ሥራ እንዲጀምሩ እየተደረገ ነው፤ የአላማጣ ገበያም ወደ መደበኛ ሥራው ተመልሷል ብለዋል።

እንደ አቶ ኃይሉ ማብራሪያ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ወደነበረበት ተመልሷል።

ወደ ሁሉም የራያ ወረዳዎች የሚደረገውን የትራንስፖርት አገልግሎት ጨምሮ በከተማ ውስጥ ባጃጆች ወደ ቀደመ ሥራቸው ተመልሰዋል። ጤና ጣቢያዎች ሥራ ጀምረዋል።

ከሦስት ትምህርት ቤቶች በስተቀር ትምህርት ተጀምሯል ያሉት ከንቲባው፣ ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ የቀሩ ሦስት ትምህርት ቤቶችን በሙሉ አቅም ወደ ሥራ በማስገባት ወደነበረበት እንዲመለስ ይደረጋልም ብለዋል።

አላማጣና በዙሪያው ያሉ ወረዳዎች ላለፉት ሁለት ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ የተጐዱ ናቸው የሚሉት የከተማዋ ከንቲባ፣ የተጀመረው የሰብዓዊ ድጋፍ ሊጠናከር፣ እንደ ባንክ ዓይነት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥራ ሊጀምሩ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ከንቲባው እንዳሉት፤ የጤና ተቋማት አገልግሎት መስጫ ቁሳቁስ መሟላት አለበት፤ በትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ወንበርና የኮምፒውተር ችግር ሊቃለል ይገባል፡፡

## በዲፕሎማሲ መስክ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በኃያላን አገራት የሚዘወር በመሆኑ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ እድገት ላይ ላሉት ሀገራት ሂደቱ እጅግ ፈታኝ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በሕዳሴው ግድብና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በሀገራችን ከተከሰተው ጦርነት ጋር ተያይዞ የተደቀነባት ጫናና ጣልቃ ገብነትን ለመግታት ከኃያላን ሀገራት ጋር ትንቅንቅ ውስጥ እንደ ነበረች ያወሱት አማካሪው፤ በእነዚህ ሀገራት ጫና አንዳንድ ሀገሮች ሲፈርሱ ኢትዮጵያ ጫናዎቹን ተቋቁማ መጓዟና ከፍተኛ ስኬት ማስመዝገቧ እንደ ቀላል የሚታይ ጉዳይ አይደለም ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የግድቡን የውሃ ሙሌት ማከናወኗ እና የሰሜኑ ጦርነት በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ሥር እንዲደረግ የያዘችው አቋም እውን መሆኑ ራሱ ትልቅ ድል ነው ያሉት አቶ ሙክታር፤ ከዚህ አንጻር ጫናውን በመጋፈጥ ያለ ማንም የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት “በችግራችን ጊዜ ከእኛ ጋር የሆኑትና እኛም በችግራቸው ጊዜ አብረናቸው በነበርነው የአፍሪካ ወንድም ሕዝቦች አማካኝነት የነበረውን ችግር መፍታት መቻል ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት ተብሎ እንደሚወሰድም አስገንዝበዋል፡፡

ስለዲፕሎማሲ ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸው አንዳንድ ወገኖች የአገሪቱን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ሲተቹ ማስተዋላቸውን የገለጹት ከፍተኛ አማካሪው፤ ዳሩ ግን ዐውዱ ከኃያላን ሀገራት ጋር በመሆኑ የተገኘው ስኬት በእጅጉ የሚመሰገን መሆኑን አመልክተዋል፡፡

እንደ አቶ ሙክታር ማብራሪያ፣ ከወሳኙ የቀይ ባሕር ቀጠና አኳያ ተፈላጊ ከሆኑት አከባቢዎች አንዷ ኢትዮጵያ ናት፡፡ በአካባቢው የኃያላን ሀገራት ፍላጎት እንደ ዓለም አቀፉ ዲፕሎማሲ ውስብስብና ተለዋዋጭ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳዩን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አንጻር በስፋትና በጥልቀት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንጻር መንግስት በዲፕሎማሲ ረገድ አዳዲስ አሰራሮች በማበጀት በሥልጠና እያዳበረ ይገኛል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በጥቅሉ አንዳንዶች እንደሚሉት የዲፕሎማሲ ስኬት በዲፕሎማቶች እውቀትና ብቃት ብቻ የሚመዘን ጉዳይ ሳይሆን በኃያላን አወንታና በውስብስብ ነባራዊ ሁኔታዎች የሚዳኝ ሥራ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

አንዳንድ ወዳጅ ሀያላን ሀገራት በኢትዮጵያ ላይ የተደረገውን ጫና በመቃወም ከኢትዮጵያ ጎን መቆማቸው፤ ዲያስፖራውን በማስተባበር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረጉ የተቃውሞና የድጋፍ እንቅስቃሴዎች፤ በሀገር ጥቅም ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ ጽኑ አቋምና ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለው መልካም ጉርብትና ተደምረው ለዲፕሎማሲው ስኬት ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውንም አቶ ሙክታር ገልጸዋል፡፡

## “የሰላም ስምምነቱን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተደረሰው የሰላም ስምምነት በኋላ በትግራይ የታዩት የመረጋጋት ሁኔታዎች ሕዝቡ ሰላምን በጉጉት ሲጠብቅ እንደነበር የሚያሳዩ መሆናቸውንም አቶ መስፍን ተናግረዋል።ትዴፓ የሰላም ስምምነቱን በደስታ በመቀበል ለተግባራዊነቱ ከተለያዩ አካላት ጋር አብሮ እንደሚሠራም ገልጿል፡፡

አቶ መስፍን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደተናገሩት፤ ለትግራይ ሕዝብ ትልቅ እፎይታን ከፈጠረው የሰላም ስምምነት ማግስት በትግራይ የታዩት የመረጋጋት እና የሰላም መንፈስ ሕዝቡ ሰላምን በከፍተኛ ጉጉት ሲጠብቅ እንደነበር የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ከስምምነቱ በኋላ በክልሉ የተከሰቱት መልካም ነገሮች ሕዝቡ ቀድሞም ከችግሮቹ ለመውጣት ጓጉቶ እንደነበር ያሳያል ያሉት አቶ መስፍን ሕዝቡ ምን ያህል በጦርነት ተማሮ እንደነበር የሚያሳይ መሆኑንም ጭምር ነው ያመላከቱት፡፡

እንደ ምክትል ሊቀመንበሩ ገለጻ፤ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በትግራይ ውስጥ የታዩ ለውጦች አሉ፤ በዚህም ከተኩስ ድምፅ እንዲሁም ከስጋት ነፃ ሆኖ በሰላም ተኝቶ ማደር ጀምሯል፣ የሸቀጦች ዋጋ መቀነስ እና በከፍተኛ ተስፋ መሞላት በሕዝቡ ላይ ከተስተዋሉ ነገሮች መሐል ጥቂቶቹ ናቸው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ችግሮችን በሰላማዊ ውይይት የመፍታት ታሪክ አልነበረም ያሉት አቶ መስፍን፣ የሰላም ስምምነቱ አዲስ ባህልና ተዓምር ነው ሊባል የሚችልና ለትግራይ ሕዝብም እፎይታን የፈጠረ ነው ብለዋል።

የተገኘው ሰላም ተጠናክሮ እንዲቀጥልና እንዳይደፈርስ ለሰላም ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ዋጋ መክፈል አለበት ያሉት ምክትል ሊቀመንበሩ፤ ለሰላም ስምምነቱ ተፈፃሚነት ከሚቆሙ አካላት ጎን መሆንና የሰላም ስምምነቱን ከፍተኛ ፋይዳ ማስጠበቅ ያሻልም ብለዋል፡፡

አንዳንድ ጽንፈኛ ዲያስፖራዎች እና ሰላም የማይፈልጉ የትግራይ አክቲቪስቶችም የተለያዩ ችግሮችን በመፍጠር እንዲሁም በያሉበት ሀገር ሰልፍ በማድረግና በተለያዩ የማኅበራዊ የትስስር ገፃቸው ላይ የሰላም ሂደቱ ተፈጻሚ እንዳይሆን ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንደሚገኙም ምክትል ሊቀመንበሩ ገልጸዋል።

አክቲቪስቶቹ ካለው ልማት ተቋዳሽ የሆኑት ያሉበት ሀገር ሰላምና ነፃነት ስላለው ነው ያሉት አቶ መስፍን፣ ስለ ሰላም ውጤት ከእነርሱ በላይ ማንም ሊያውቅ አይገባም ነበር ብለዋል።እነዚህ ሰዎች ከስሜት ወጥተው ወደ ውስጣቸው ቢያስቡ መልካም መሆኑንም መክረዋል።መከራ ውስጥ ያለው የትግራይ ሕዝብ እንዴት ከዚህ ችግር መዳን አለበት ለሚለው መፍትሔ ሊፈልጉ ይገባቸዋልም ብለዋል፡፡

ይህንን የሰላም ስምምነት ማደናቀፍ ማለት የትግራይ ሕዝብ በጦርነት አዙሪት ውስጥ ሆኖ በተደራራቢ ችግሮች ውስጥ ኑሮውን ይግፋ በሚል መፍረድ ነው ያሉት ምክትል ሊቀመንበሩ፤ ጸረ ሰላም ኃይሎችንም ማንኛውም ሰላም ፈላጊ ሕዝብ ሊዋጋቸው እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

የሰላም ስምምነቱን የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ በደስታ የተቀበለው ሲሆን ለተግባራዊነቱም ከተለያዩ አካላት ጋር አብሮ እንደሚሠራ አቶ መስፍን ገልጸዋል፡፡

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ሲያሰሙ አልታየም ብለዋል፡፡

በሁሉም ኢንዱስትሪዎች የግብርና ጥሬ ዕቃዎች እጥረት እንደማይታይ የገለጹት ሚኒስትሩ፤በዘይት፤ በጨርቃጨርቅ፤ በስጋ ፋብሪካዎች የሚታየውን የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር ለመቅረፍም በአኩሪ አተር፣በጥጥና በእንስሳት ልማት ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ሁለቱ ሴክተሮች በቅንጅት እየሠሩ በመሆናቸው የኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግርም በሂደት እየተሻሻለ ይሄዳል ብለዋል፡፡

ከመንግሥት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የፋብሪካ ባለቤቶች የጥሬ ዕቃ ችግሮቿቸውን በዘላቂነት ለመፍታትም ከአርሶ አደሩ ጋር በመዋዋል ምርቱን በጥራትና በብዛት የሚረከቡበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚጠበቅባቸው አመልክተው፤ ግብርና ሚኒስቴር ችግሩን ለመፍታት የኩታ ገጠም እርሻ እሳቤን ተግባራዊ ማድረጉንና በአሁኑ ጊዜም በኩታ ገጠም የሚሸፍን የእርሻ መሬት 47 በመቶ መድረሱን ተናግረዋል፡፡

በየዓመቱ የኩታ ገጠም እርሻን እያስፋፉንና የምርት ጥራቱን እየተጠበቀ ሲሄድም የኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ ፍላጎታቸውን የመሸፈን አቅማችን እየጨመረ እንደሚሄድ ጠቁመዋል፡፡

ግብርናው ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን ጥሬ ዕቃ ለማሟላት እሱም መደገፍ እንደሚኖርበት ገልጸው፤በተለይ ባንኮች ወደ አርሶ አደሩ ቀርበው ፋይናንስ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ቢኖርና ፋብሪካ ያላቸው ሰዎች ወደ አርሶ አደሩ ሄደው ውል ገብተው የሚፈልጉትን ምረት ማስመረት የሚችሉበት ሁኔታ ቢፈጥሩ ችግሩን በቀላሉ መቅረፍ እንደሚቻል አመልክተዋል፡፡

ለምሳሌም ቢራ ፋብሪካዎች ገብስ ከሚያመርተው አርሶ አደር ጋር ውል ገብተው ገብስ የሚያስመርቱበት ሁኔታ መኖሩን ጠቅሰው፤ይህን አሠራር በሌሎች ማስፋፋት ቢቻል የፋብሪካዎች የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግሮቻቸው እየተፈታ የሚሄድ መሆኑን አቶ ዑመር ጠቁመዋል

ኢንዱስትሪና ግብርና ሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች ከዕቅድ ጀምሮ እስከ አተገባበር ድረስ በቅንጅት እየሠሩ ነው ያሉት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፤ በዚህም ለአብነት 144ሺህ አርሶ አደሮችን ከኢንዱስትሪዎች ጋር የማስተሳሰር ሥራ መሠራቱን ጠቅሰዋል፡፡

የጨርቃ ጨርቅና የቢራ ፋብሪካዎችን የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር ለመፍታትም የጥጥና የገብስ ባለፈው ዓመት የተመረተው የምርት መጠንና ዘንድሮ የተሸፈነው መሬት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው፤ሁለቱ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በቅንጅት የኢንዱስትሪዎችን የጥሬ ዕቃ ችግሮች ለመፍታት ባለፉት ሦስት ዓመታት በሠሩት ሥራ ውጤቶች እየመጣ ነው ብለዋል፡፡

የዘይት ፋብሪካዎች ካላቸው የማምረት አቅም በጥሬ ዕቃ ችግር ምክንያት የሚያመርቱት እስከ 36 በመቶ ድረስ መሆኑን አውስተው፤ባለፈው ዓመት ብዙ መሬት በዘይት ጥሬ ዕቃ በሚሆኑ ምርቶች በመሸፈኑ ከፍተኛ መሻሻል እንደሚኖርም ጠቁመዋል።ለአብነትም ባለፈው ዓመት በአንድ ክልል ብቻ 242 ሄክታር መሬት አኩሪ አተር ተሸፍኗል ነው ያሉት፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎቹ የግብዓት ችግሮቻቸው ሙሉ ለሙሉ ተፈትተዋል ባይባልም ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች እየታዩ ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ሁለቱ ተቋማት ከዕቅድ ጀምሮ አፈጻጸማቸው ተከታታይነት ባለው መልኩ እየገመገሙ መሄዳቸው የኢንዱስትሪ ፋብሪካዎች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግራቸው እየተፈታ እንዲሄድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ብለዋል፡፡

አሁንም ከጥራትና ብዛት ያለው ምርት ከማቅረብ አኳያ ብዙ ሥራ መሥራት እንደሚጠይቅ ጠቁመው፤ አሁንም ደላላዎች በሚያደርጉት ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ በአርሶ አደሩና አምራች ፋብሪካዎች በተመጣጣኝ ዋጋና ምርት እንዳያገኙ እያደረገ በመሆኑ ይህንና መሰል ችግሮችን በጋራ ለመፍታት የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## እየተደረገ ያለው የሰብዓዊ እርዳታና የመልሶ ግንባታ ሥራ መንግሥት ለሰላም ስምምነቱ እውን መሆን ያለው ቁርጠኝነት ማሳያ ነው!

በፌደራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ዘላቂ ሰላም በሀገራችን ለማረጋገጥ የሚረዳ በመሆኑ ስምምነቱ ወደ መሬት እንዲወርድ መንግሥት ለተግባራዊነቱ በቁርጠኝነት እየሠራ ነው። የሰላም ስምምነት ከተደረሰበት ዕለት ጀምሮ በሰላም ዙሪያ ሳይታክት እየሠራ ይገኛል። ቀደም ሲል ጀምሮ የሰላም እጆቹን ዘርግቶ ስለ ሰላም ሲተጋ የቆየው መንግሥት አሁንም የሰላም ስምምነቱ መሬት እንዲነካና ከሰላሙ ሕዝብም ሀገርም ተጠቃሚ እንዲሆኑ በቁርጠኝነት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

ሰላምን በሀገር ላይ ከማስፈኑ ጎን ለጎንም ለሰብዓዊ እርዳታና የወደሙ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መልሶ በመገንባት ሥራ ተጠምዷል። በተለይም በትግራይ ክልል ላሉ ተረጂዎች የሰብዓዊ እርዳታ በብዛት እና በስፋት እንዲደርስ የማድረጉ ሥራ ትኩረት ሰጥቶ ሲሠራበት ቆይቷል። አሁንም እየተሠራበት ቀጥሏል። አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆን በየአቅጣጫው ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ ሲሆን ለዚህም ድጋፉ በየብስና በአየር ጭምር እንዲገባ ተደርጓል።

እስካሁን ባለው ሁኔታ በትግራይ ክልል 7 ሺህ 523 ሜትሪክ ቶን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ እቃዎች እንዲሁም 364 ሜትሪክ ቶን መድኃኒት መሰራጨቱን ሰሞኑን የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታውቋል፡፡

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ወደ ትግራይ ክልል የሚገቡ የተለያዩ የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦቶች ተጠናክረው መቀጠላቸውን አንስቷል፡፡ በዚህ መሠረት እስከ ኅዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም በ198 ተሽከርካሪ 6 ሺህ 93 ነጥብ 4 ሜትሪክ ቶን ምግብና አልሚ ምግብ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች ተሰራጭቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 364 ሜትሪክ ቶን መድኃኒት፣ 105 ሺህ 159 ሊትር ነዳጅ እና 1 ሺህ 74 ነጥብ 6 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ እቃዎች የማሰራጨት ሥራ ተሠርቷል።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በትግራይ ክልል የተጀመረው ያልተገደበ የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭትም በመንግሥትም ሆነ በአጋር አካላት ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን ለስኬታማነቱም ሁሉም ሕዝብ እንዲሁም አጋር ድርጅቶች ሊረባረቡ ይገባል።

የሰብዓዊ እርዳታውን በማሰራጨት በኩልም ከመንግሥት ጋር አጋር አካላት እየሠሩ ሲሆን በእስካሁኑ ሂደትም 11 አጋር አካላት ተሳታፊ ሆነዋል። ።የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ፣ አፋርና አማራ ክልል እያደረገ ያለውን ያልተገደበ ሰብዓዊ ድጋፍ የማቅረብና መሠረተ ልማቶችን መልሶ የመገንባት ጥረት አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል። ይሁን እንጂ ሰብዓዊ እርዳታውም ሆነ የመልሶ ግንባታ ሥራው በመንግሥት አቅም ብቻ ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ ይሆናል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። በመሆኑ ለጋሽ ድርጅቶች ፣ ዲያስፖራዎች እንዲሁም ዜጎች አስፈላጊውን እገዛና ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ከሰብዓዊ እርዳታው ጎን ለጎንም በጦርነቱ ምክንያት በመቀሌ፣ አማራና አፋር ክልሎች የወደሙ የመሠረተ ልማቶችን መልሶ መገንባት ሥራም ትኩረት የተሰጠው ሲሆን በዚሁ መሠረት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተቋርጦባቸው የነበሩ አካባቢዎች መብራት እንዲያገኙ ሆነዋል። እንዲሁም ኤሌክትሪክ ያላገኙ አካባቢዎች ደግሞ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመልሶ ግንባታው ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው። በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን መንገዶችና ድልድዮች መልሶ በመገንባት የሰብዓዊ እርዳታው በተሳለጠ መንገድ እንዲጓዝ ጭምር እየተሠራ ይገኛል። የቴሌኮምና የባንክ አገልግሎቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ያልተቋረጠ ጥረት እየተደረገ ነው ።

እንዲሁም ሰብዓዊ እርዳታው በፍጥነት እንዲደርስም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ትግራይ ክልል ተቋርጦ የቆየውን መደበኛ በረራ ለመጀመር በዝግጅት ላይ መሆኑን አስታውቋል። ይህም የሰብዓዊ ድጋፍ ተደራሽነትን ለማቀላጠፍና ለማፋጠን የሚያግዝ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ መደበኛ አገልግሎት ይሰጣል። በአሁኑ ወቅት በክልሉ ከሚገኙ ኤርፖርቶች መካከል የመቀሌ እና የሽሬ አየር ማረፊያ ጥሩና ለበረራ ምቹ ሲሆኑ የአክሱም ኤርፖርት ግን በግጭቱ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ለበረራ በሚመች መልኩ ማስተካከያ የሚደረግለት መሆኑ ተገልጿል።

የሰላም ስምምነቱ ወደ መሬት ወርዶ ሀገርም ዜጋውም ተጠቃሚ እንዲሆን በየአቅጣጫው የተጀመረው ሥራ በተለያየ መስኩ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ለዚህም መንግሥት የመሪነቱን ሚና እየተወጣና ውጤቱም በተግባር እየታየ ነው። ሰላም ለሁሉም አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ለሰላም በሁሉም በኩል ትልቅ መስዋዕትነት መክፈል ይገባል። ዛሬ የሰብዓዊ ድጋፉ ለተረጂዎች እየደረሰ ያለው ተኩስ በመቆሙና አንጻራዊ ሰላም በመስፈኑ ምክንያት ነው። በመሆኑም ለዘላቂ ሰላም ሳይታክቱ መሠራት ያስፈልጋል፤ ይገባልም!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# በኅዳሩ ጭስ ችግር መከራችን ይራቅ

**በእምነት**

እ.ኤ.አ ከ 1914 እስከ 1918 ዓ.ም ድረስ የዘለቀውና የ15 ሚሊዮን ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈው ጦርነት በታሪክ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ተብሎ ይታወቃል። የጦርነቱ ማብቃት ሊታወጅ ጥቂት ሲቀረውና ዕልቂቱ ቆመ ሲባል ግን የዓለም ሕዝብ ሌላ ፍዳ ማስተናገድ ግድ ሆነበት። በጦርነት ተወጥሮ የቆየው ዓለም አሁን ደግሞ በእንፍሉዌንዛ በሽታ ከዳር እስከ ዳር ተጠቃ። በተለምዶ የእስፓኒሽ ፍሉ ተብሎ የሚታወቀው ይህ ወረርሽኝ መነሻው ከወደ አሜሪካ እንደሆነ ይታመናል። ይህም እ.ኤ.አ በጥር ወር 1918 ዓ.ም በአንደኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ዋዜማ የተከሰተው ወረርሽኝ በመሆንም ለበርካቶች ሞት ምክንያት ሆኗል።

የታሪክ ድርሳናት ስለዚህ ወረርሽኝ ሲገልጹ በካንሳስ በሚገኘው ፉንስተን የወታደራዊ ማሰልጠኛ ማዕከል የተቀሰቀሰው ወረርሽኙ በሦስት ቀናት ብቻ 45 ሺህ የሚሆኑ ወታደሮችን ጨርሷል፤ የተረፉትም አትላንቲክን አቋርጠው አውሮፓን እንደረገጡ በሽታውም አውሮፓ ስለመድረሱ ይነገራል። የእንፍሉዌንዛ በሽታው ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው በፈረንሳይ አገር ቢሆንም ወቅቱ የጦርነት ነበርና ለሌሎች የፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ ይሆናል በሚል ለሕዝብ ሳይገለጽ ተደብቆ ቆይቷል። በሽታው ይፋ የሆነው እ.ኤ.አ በኅዳር ወር 1918 ዓ.ም በስፔን አገር ነበር።

ስፔን በጦርነቱ ተካፋይ አልነበረችምና የተከሰተባትን ችግር በቶሎ ይፋ አደረገችው። በቶሎ ይፋ ማድረጓ ደግሞ በሽታው «ስፓኒሽ ፍሉ» የሚል ስያሜንም እንዲይዝ አድርጎታል፤ አሁን ዓለም ከጦርነት ወደ በሽታ ፊቱን አዞረ፤ መገናኛ ብዙኃኑ ሁሉ ስለተከሰተው በሽታ በስፋት ዘገቡ፤ አወሩ። ምን ይደረግ የሚለው ነገርም በእጅጉ አሳሳቢ ነበር። ወረርሺኙም ዓለም ላይ ለመዛመት ብዙም ጊዜ አልፈጀበትም። በኢትዮጵያም በሽታው መታየት ጀመረ። የመጀመሪያው የበሽታው ምልክት በዓለም ላይ ከታየ ከአስር ወር በኋላ ኢትዮጵያ ደረሰ። ኢትዮጵያም ችግሩ እንዳጋጠማት በኅዳር ወር 1911 ዓ.ም ይፋ አደረገች።

በዚህም ከኅዳር 7 እስከ ኅዳር 20 ቀን 1911 ዓ.ም ለአስራ አራት ቀናት ገደማ የቆየው በሽታው ብዙዎችን ፈጀ። ወረርሽኙ እስከ አርባ ሺህ ኢትዮጵያውንን ለሞት መዳረጉ ይነገርለታል፤ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ዘጠኝ ሺህ ዜጎች በበሽታው መሞታቸውንም ነው መረጃዎች የሚያመለክቱት። በተለይም ኅዳር 12 ቀን 1911 ዓ.ም በርካታ ኢትዮጵያውያን የሞቱበት ስለመሆኑም ታሪክ ያወራል። ታዲያ ኢትዮጵያውያን በየወቅቱ ለሚገጥሟቸው ችግሮች ሁሉ መፍትሔ አያጡምና ይህንን በሽታ እንዴት እንለፈው? ሲሉ መከሩ፤ በምክክራቸውም ብቸኛው ያገኙት መላ ደግሞ ሁሉም ከየቤቱና ከአካባቢው ቆሻሻን በመሰብሰብ እንዲያቃጥል፤ በጠቅላላው ቤቱንና አካባቢውን ጽዱ እንዲያደርግ የሚል ነበር።

በዚህም ኅዳር 12 ቀን በጽዳት ዘመቻ እንዲያልፍ በአዋጅ ተነገረ፣ ኅዳር በታጠነ ማግስትም በሽታው ጋብ አለ። በሂደትም ወደ መጥፋቱ ሄደ። ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ይህ ነገር እንደባህል ተወስዶ በየዓመቱ ኅዳር 12 ቀን የጽዳት ዘመቻ እየተደረገ ሁሉም በየአካባቢው ቆሻሻን ሰብስቦ እያቃጠለ ችግሩንም፣ በሽታውንም፤ በጠቅላላው መጥፎ ነገሮችን ሁሉ ከጭሱ ጋር ብን ብለው እንዲጠፉ እየተመኘ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

አዎ ዛሬ ላይ ቆሜ እኔም ለአገሬ የምመኝላት ከኅዳሩ ጭስ ጋር ችግሮቿ ብን ብለው እንዲጠፉ፤ የእሷን መጥፋት የሕዝቦቿን መበተን የሚመኙ ሁሉ ከጭሱ በኋላ ሀሳባቸው ብን እንዲል ነው። ወትሮም ቢሆን ለችግሮቻችን ራሳችን መፍትሔ ማስቀመጥ የማይሳነን እኛ ዛሬም ለተፈጠረብን ወደፊትም ሊፈጠርብን ለሚችለው ችግር ሁሉ ከዛሬ 104 ዓመት በፊት የወሰድነውን ዓይነት መፍትሔ መውሰድ ይገባናል።

በእርግጥ ችግራችንን በራሳችን አቅም ለመፍታት የምንችል ሕዝቦች መሆናችንን ባለፉት ሁለት አመታት በተፈጠረብን ችግር አሳይተናል። አሁን ላይ ያለንን አቅም የዓለም ኃያላን ነን ባዮችም የተገነዘቡት ይመስለኛል። የሰላም አማራጭን ከመረጥን በኋላም ቢሆን እኛ ካልገባንበት እናንተ ለራሳችሁ ሰላም ማምጣት አትችሉም በማለት ያሾፉብንንም ጥቂት አፍሪካውያን ወዳጆቻችንን ይዘን በድል አጠናቀነዋል፤ ምክንያቱም ሲወርድ ሲዋረድ አብሮን የቆየ ችግር መፍቻ ብልሃት ስላለን ነው። አሁንም ይህ አቅማችን በደንብ ዳብሮ የሄድንበት ርቀትም መስመር ይዞ ይቅርታና ሰላማችን ከልባችን ሆኖ ስለልጆቻችን ብለን መጪውን ጊዜያችንን ብሩህ ማድረግ ይገባናል።

ከዛሬ 104 ዓመት በፊት አቅም ያላቸውን የዓለም አገራትን እንኳን ፈትኖ ያልቻሉት በሽታ አገራችንም ገብቶ ሕዝብን ሊፈጅ አገርን ባዶ ሊያስቀር ቆርጦ ሲነሳ ብልሆቹ የእኛዎቹ ኢትዮጵያውያን እናትና አባቶቻችን በብልሃት ችግሩን እኛው በእኛው ብለው በወሰኑት መሠረት ኅዳርን አጥነው በጭስ አስፈሪውን ደዌ አባረውታል፤ መጥፎውን ጊዜም በድል ተወጥተውታል። ይህ አኩሪ ነገር እነሆ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል።

ኅዳር ሲታጠን...

የኢትዮጵያ ሰማይ በበረከት ይታወድ...

በምድሯም ሁሉ የምር የሆነ እርቅ ይውረድ...!

አሜን...! አሜን..! ይሁን...!

እያልን የምር የሆነውን እርቃችንን ከልባችን አውርደን አገራችንን ወደፊት የምትሄድበትን መንገድ ማመቻቸቱ ደግሞ ከእኛ ከዛሬዎቹ ተማርን ተመራመርን አወቅን መጠቅን ከምንለው ልጆቿ የሚጠበቅ ነገር ነው።

ኅዳር ወር ሲታጠን ችግር መከራው ይሄዳል፤ ይህንንም ታሪክ አስተምሮናል። ከኅዳር ቀጥሎ የሚመጡት ወራቶች ደግሞ የሚያጓጉ ምድር በረከቷን አብዝታ የምትሰጥበት በጠቅላላው ጥጋብ በምድር ላይ የሚሰፍንበት ስለመሆኑ ደግሞ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ የሚያውቀው ሃቅ ነው። ታዲያ ኅዳርን አጥነን ችግራችንን አባረን የዘራነውን አጭደን ከምረን ወቅተንና ጎተራ ከተን ሰርግ ደግሰን ዘመድ አዝማድ ጠርተን ብሉልኝ ጠጡልኝ የምንባባልበት ሁኔታ ይፈጠር ዘንድ እርቃችንን የምር እናድርገው።

ዛሬ አገር የደከመች፣ እኛም የተጣላን መስሏቸው በእሳት ላይ ቤንዚን ለማርከፍከፍ ደፋ ቀና የሚሉቱ ምን ብናደርግ ይታመሳሉ ብለው እንቅልፍ የሚያጡት ባሳየናቸው አንድነትና ሰላም ወዳድነት አንገታቸውን ደፍተዋል። ነገር ግን እነዚህ ኃያላን ሽንፈታቸውን አምነው የሚቀመጡም አይደሉምና አሁንም ነቅተን እርቃችንን ከልባችን አድርገን ማሳየት ይገባናል። ያን ጊዜ እንደልባችን መንጻት ሆኖ የኅዳር ጭስ ችግራችንን ይዞ ብን ይላል። አበቃሁ፤

**ሰላም!**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## አገር በፖለቲካ ብቻ አትበለጽግም፤ በሳይንስም ጭምር እንጂ

ይበል ካሳ

በአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገት ውስጥ ፖለቲካ ወይንም የሥነ መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር እሳቤዎችና ዘየዎች የአንበሳውን ድርሻ የሚይዙ ስለመሆናቸው ብዙኃኑ ጠቢባን የሚስማሙበት ሃቅ ነው። ይሁን እንጂ ሌሎች የፍልስፍናና የዕውቀት ዓይነቶች፣ ጥበቦች፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀቶችና ሥራዎች ለአገር ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ የዚያኑ ያህል ተፈላጊና አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ከፖለቲካው ባሻገር ሳይንስና ቴክኖሎጂን ሌሎችም ዕውቀቶች ለአገር ዕድገት ያላቸውን ሚና አስመልክቶ የሃሳብ ተጋሪዬ የሆኑት ዶክተር በፍቃዱ ኃይሉ እንዲህ ይላሉ፡-

"....እንደሚታወቀው አገራችን ላለችበት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰብአዊ፣ የሥነ-ልቦናና የባህል ችግር፣ እንዲሁም የፖለቲካና የርዕይ ችግር የብሔረሰብ መብትን በማወቅ የሚፈታ ነገር አይደለም። የአገራችን ችግሮች ፖለቲካዊ፣ መንግሥታዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የአካባቢ መውደም ወይም መቆሸሽ ጉዳይና እንዲሁም የሳይንስና የቴክኖሎጂ ጥያቄዎች እንደመሆናቸው መጠን ጠቅላላውን፣ በዚያች ምድር የሚኖረውን ሕዝብ የሚመለከቱ ናቸው። ይህም ማለት ያሉት ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት፣ በፍልስፍና፣ በሶስዮሎጂ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም በሁለ-ገብ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አማካይነት ብቻ ነው።

በሌላ አነጋገር፣ በአገራችን ምድር አፍጠው አግጠው የሚታዩት ችግሮች፣ ማለትም የከተሞች በሥነ-ሥርዓት አለመገንባትና ሕዝባችንም ባልባሌ ቦታዎች እየተሰቃየ መኖር፣ የሚጠጣው፣ የሚቀቅልበትና የሚታጠብበት ንጹህ ውሃ አለማግኘት፣ አስፈላጊው ለሰውነት ገንቢ የሆኑ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን በብዛትም ሆነ በጥራት አለማግኘት፣ ለማሞቂያ፣ ለመቀቀያና ለመብራት የሚያገለግል የኃይል ጉዳይ፣ የሕክምናና የትምህርት ጉዳይ፣ ለወጣቱ የሙያ ማሰልጠኛ ቦታ አለማግኘት፣ በየቦታው የሥራ መስክ የሚከፍቱ ትናንሽና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች አለመኖር... ወዘተ እነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ ኅብረተሰብአዊ እንደመሆናቸው መጠን የብሔረሰብን መብት በማወቅ የሚፈቱ ሳይሆኑ፣ በጠለቀና ተከታታይነት ባለው የሳይንስ ምርምር ብቻ ነው። ሊያሠራ የሚችል፣ ኃይልን የሚሰበስብና በአገር ውስጥ ያለን የተፈጥሮ ሀብት በሥነሥርዓት አውጥተን በቴክኖሎጂ አማካይነት ለመለወጥና የሕዝባችንን ፍላጎቶች ለመመለስ የምንችለው አንዳች ዓይነት ርዕይ ሲኖረን ብቻ ነው። "

ታዋቂው የኢንተርፕርነር ምሁር አሰልጣኝና ደራሲ ዶክተር ወሮታው በዛብህ በአንድ ወቅት ለተማሪዎች የምረቃ ሥነ ሥርዓት በተዘጋጀ መድረክ ላይ አሜሪካ የምትባለውን ኃያል አገር በመገንባት ሂደት ውስጥ ከፖለቲከኞች በላይ ሳይንቲስቶች፣ ምሁራንና ኢንተርፕርነሮች የነበራቸው ሚና የጎላ መሆኑን ተናግረዋል። እንዲያውም ኃያሏን አሜሪካ የፈጠሯት እንደ ቬንደር ቬልት፣ ጂ.ኬ ሞርጋንና አንድሬው ካርኒጌ የመሳሰሉ በከፍተኛ ደረጃ በሥራ ፈጠራ የተካኑ ጥቂት ግለሰቦች መሆናቸውን "ሜን ሁ ቢዩልት አሜሪካ" የሚል የፊልም ሥራን በማስረጃነት በመጥቀስ በአንድ ግንባታ ሂደት ውስጥ ከፖለቲካ ውጪ የሆኑ ዕውቀቶች ያላቸውን ከፍተኛ ዋጋ አስረድተዋል።

የእኔ አመለካከትም ከዚሁ ብዙ የሚርቅ ስላልሆነ ነው ይህን ጽሑፍ የምጽፈው። ምናልባት ከዶክተር ወረታው የምለየበት ምክንያት ለአገር ግንባታ ፖለቲከኞችም ምሁራንም እኩል ሚና አላቸው ብዬ የማምን በመሆኔ ነው። ሁሉም ሰው በያለበት ሙያ ለአገሩ ትልቅ ሥራ መሥራት ይችላል ብዬ አስባለሁ። ፖለቲካንም ሳይንስንም ማናቸውም ቢሆኑ አገርን የሚጠቅሙ ነገሮችን ሁሉ እኩል መውደድ ይገባናል ብዬ አምናለሁ። እናም እኩል ትኩረት ልንሰጣቸው፣ ልናወራላቸው፣ ልንጽፍላቸው ይገባል ብዬ አስባለሁ! ከፖለቲካ ውጪ ያሉ ዕውቀቶች ለአገር ዕድገት ያላቸው አስተዋፅኦ ለማይታያችሁና አገር በፖለቲካ ብቻ የምትኖር ለምትመስላችሁ ወገኖቼ «ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ በሚወጣ ኃይል ጭምር እንጂ አገር በፖለቲካ ብቻ አትኖርም» ልላችሁ እወዳለሁ።

ከዚህ አኳያ ስንመለከተው የጠፈር ምርምር ሳይንስ (Space Science) በተለይም ደግሞ በዘርፉ ምሁራን ዘንድ «የጠፈር ሳይንስ ልብ» በመባል የሚወደሰው

> **የዘርፉ ምሁራንና ባለሙያዎች እንደሚያስገነዝቡት የህዋ ሳይንስ በማንኛውም የልማት ዓይነት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልና በትልቁ ከሰው ሕይወት ጋር የተቆራኘ ሁለንተናዊ ፋይዳ ያለው ሳይንስ ነው። ሆኖም የእኛን አገር ጨምሮ በሌሎችም የሳይንሱ ፋይዳ ባልተገለጸላቸው ታዳጊ አገራት በብዙዎች ዘንድ የህዋ ሳይንስ ለድሃ አገራት አያስፈልግም የሚል የተሳሳተ አመለካከት አለ**

የሳተላይት ቴክኖሎጂና ሳይንስ በማንኛውም ዘርፍ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልና በአገር ሁለንተናዊ ዕድገት ውስጥ ቁልፍ ሚና ሊጫወት የሚችል ተመንዝሮ የማያልቅ ፋይዳ ያለው ተግባራዊ ሳይንስ ነው። የሳተላይት ቴክኖሎጂ በአየር ትንበያ መረጃና በግብርና፣ በምህንድስና፣ በመረጃና በቴሌ ኮምዩኒኬሽን፣ በከተማ ልማት፣ በኢንዱስትሪ፣ በውትድርና ሳይንስና በአገር ደህንነት፣ በሕክምናና በጤና፣ በትምህርትና ማህበራዊ ለውጥ፣ በአየር ንብረት ብክለት ቁጥጥርና በአካባቢ ጥበቃ፣... በአጠቃላይ በሁሉም የልማት መስኮች ውስጥ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸው ዕውቀቶች የሚገኙበት ከሁሉም በላይ ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው የተግባር ሳይንስ ነው። ይህም በአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁለንተናዊ ዕድገት ቁልፍ ሚናን ይጫወታል።

ታዲያ ከዚህ ጋር በተያያዘ ታኅሣሥ 10 ቀን 2012 ዓ.ም አገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ወደጠፈር ያመጠቀቻት ETRSS-1 የመሬት ምልከታ ሳተላይት ተልዕኮዋን በአግባቡ መወጣት መቻሏንና ሳተላይቷ ከታቀደላት ጊዜ በላይ አገልግሎት እየሰጠች የምትገኝ መሆኗን የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ከሰሞኑ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጠው መግለጫ ማስታወቁ ይታወሳል። በኢትዮጵያውያንና ቻይናውያን ኢንጅነሮች በትብብር የተፈበረከችውና ታኅሣሥ 10 ቀን 2012 ከቻይና ምድር ወደ ጠፈር የመጠቀችው «የምድር ምልከታ» ከሚባሉት የሳተላይት ዓይነቶች የምትመደበው ይህችው ታሪካዊት የኢትዮጵያ ሳተላይት፤ በዚህ መልኩ ተልዕኮዋን በስኬት ማከናወኗ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሁለንተናዊ እድገት ትልቅ ትርጉም አለው።

ምክንያቱም የሳተላይቷ ዋነኛ ተልዕኮ የአገሪቱ የጀርባ አጥንት የሆነውን የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማዘመን የሚያግዙ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው። በእስካሁኑ ሙከራም ያልተሳካውን ግብርናውን የማዘመንና የዘርፉን ትራንስፎርሜሽን ሂደት ዕውን ለማድረግ በሚደረገው ርብርብ ውስጥ ትልቅ ፋይዳ አለው። የግብርናው መዘመንና የኢኮኖሚ ሽግግሩ ዕውን መሆን በበኩሉ ዜጎችን ከድህነትና ከኋላቀርነት ለማላቀቅና የሚፈለገውን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማምጣት የሚያስችል አቅም ይፈጥራል።

ይሁን እንጂ ሁሉም ነገር ፖለቲካ እየሆነ በተቸገርንባት የድህረ 1983ቷ ኢትዮጵያችን ከፖለቲካ ውጪ ሌላ ሕይወት የሌለ እስኪመስል ድረስ በጓዳም በጎዳናም፣ በቤትም በመስሪያ ቤትም፣ በቀጥታም በሚዲያም አየሩን ሁሉ የተቆጣጠረው ፖለቲካው በመሆኑ ጉዳዩ በሚገባው ልክ ትኩረት ሳይሰጠው መቅረቱን በግሌ ታዝቤያለሁ። አዎ አሁን ላይ በእኛ አገር በዋናውም ይሁን በማህበራዊ (ፖለቲካዊ ሚዲያ ቢባል ይቀላል) ሚዲያው ሰፊውን ቦታ የያዙት ፖለቲካዊ አለያም በግዴታም ቢሆን ፖለቲካ እንዲሆኑ የተደረጉ ጉዳዮች ናቸው። የሚወራውም የሚጻፈውም ከፖለቲካዊ አንድምታው አኳያ እየታየ ሆኗል። በእርግጥ ይህ ለምን እንደሆነ "ሆነ" ከማለት ባሻገር ሁሉም ነገር ፖለቲካ እየሆነ የመጣበትንና ሁሉም ፖለቲከኛ የሆነበትን ምክንያት በዚሁ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ መጻፌን አስታውሳለሁ።

ዛሬ በድጋሜ ያነሳሁት በጉዳዩ ላይ ልጽፍበት ሳይሆን ከፖለቲካው ባሻገር ልናወራላቸውና ልንጽፍላቸው የሚገቡ ሌሎችም በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን ለማስታወስና የበኩሌን በተግባር አድርጌ ለማሳየት ነው። ያኔ ከሁለት ዓመት ተኩል በፊት ሳተላይቷ ወደጠፈር በመጠቀችበት ወቅትም ጉዳዩ የፖለቲካውን ያህል ሽፋን እንዳላገኘ አስታውሳለሁ። ከርዕሰ ጉዳዩ ትልቅነት እና ታሪካዊነት አኳያ በቂ የሚዲያ ሽፋን አለማግኘቱና ሰፊ የመወያያ አጀንዳ አለመሆኑ በእጅጉ እንድገረም አድርጎኝ እንደነበረም አስታውሰሁ። በጊዜው ትዝብቴንም በዚሁ ጋዜጣ ትዝብት አምድ ላይ ጽፌያለሁ።

ምን ያህል ፖለቲካው እንደተጫነንና ሌላ ነገር እንዳናስብ አዕምሯችንን በቁጥጥሩ ስር አውሎ በእኛ ሳይሆን በእርሱ ፍላጎት እየመራን (እየነዳን ቢባል ይቀላል) መሆኑን በመታዘቤ በጉዳዩ ላይ የራሴን ምልከታ ለማካፈል ዛሬም በድጋሜ ብዕሬን እንዳነሳ ተገድጃለሁ በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ ጉዳዩ ፖለቲካ ነክ ከሆነ ትንሿን ነገር ሳይቀር እያጋነነ፣ የማይገናኘውን በግድ አገናኝቶ ፖለቲካ እያደረገ፣ እየጮኸና እያስጮኸ አገር ምድሩን ሲያዳርሰው የሚውለው «ማህበራዊ ሚዲያ» ተብየው ኢትዮጵያ ያመጠቀቻት ሳተላይት ተልዕኮዋን በስኬት ስለማከናወኗ ስለሚገልጸው ዜና ያን ያህል ሲጨነቅ አለመታየቱ ነው።

በጥፋት ንግድና ሰው ማባላት የሆነ እንደሆን ናይጀሪያ ውስጥ የሆነውን ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ ለማስመሰል ዓይኑ እስኪፈዝ ድረስ «አዶቤ» ላይ አፍጥጦ የሚውለውና አገር ምድሩን በ«ፎቶ በተደገፈ ዜና» የሚያጥለቀልቀው ማህበራዊ ሚዲያ፤ የዚህ ጊዜ መናገር ተስኖት አይጥ የዋጠች ድመት ሆኖ ጥጉን ይዞ ሲቁለጨለጭ መሰንበቱ አጃኢብ የሚያስብል ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የሆነውን ሳተላይት ወደ ህዋ እንደምታመጥቅ የሚያበስረው ዜና መሰማቱን ተከትሎ በጥቂቱም ቢሆን በተሰወኑ አካላት ዘንድ የመወያያ ርዕስ ሆኖ ቢነሳ እንኳን የሚነሱት ጉዳዮች በአብዛኛው ትችትን ያዘሉ መሆናቸው ደግሞ ያኔም ዛሬም የበለጠ ግርምትን ስለፈጠረብኝ «ግን ለምን?» የሚል ጥያቄን አጭሮብኛል። እናም ጉዳዩን በሚመለከት እኔም የራሴን ምልከታ እንዳቀርብ ምክንያት ሆኖኛል።

በዚህ ረገድ ሲቀርቡ ከታዘብኳቸው ዕውቀት ጎደል ትችቶች መካከል «ብዙ ችግር ባለባት አገር ውስጥ(የአገሪቱን ፖለቲካ ሁኔታ በዋነኝነት ያነሳሉ) በተጨማሪም በልቶ ማደር እንኳን አስቸጋሪ በሆነባት ድሃ አገር የህዋ ሳይንስ ያን ያህል አስፈላጊ ነገር ነውን? «ስንት መቅደም የሚገባቸው ነገሮች እያሉ በአሁኑ ሰዓት ሳተላይት ማምጠቅ ይህን ያህል ትኩረት ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነውን? ሳይንሱ ውድ ከመሆኑ የተነሳ ከሚያስወጣው ወጪ አኳያ እንደ አገር የሚያስገኘው ጥቅም፣ አጠቃላይ ፋይዳውስ ምንድነው?» የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው።

ሆኖም ትችቶቹ የስፔስ ሳይንስን ሁለንተናዊ ፋይዳ ያልተገነዘቡና ዕውቀት የጎደላቸው መሆናቸውን ማስገንዘብ ይገባል። እናም እዚህ ላይ የሚቀርበው ትችት ለአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገት ከፖለቲካ በተጨማሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂም እጅግ ወሳኝ ነገር መሆኑን ግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ ነው። ምክንያቱም የዘርፉ ምሁራንና ባለሙያዎች እንደሚያስገነዝቡት የህዋ ሳይንስ በማንኛውም የልማት ዓይነት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልና በትልቁ ከሰው ሕይወት ጋር የተቆራኘ ሁለንተናዊ ፋይዳ ያለው ሳይንስ ነው። ሆኖም የእኛን አገር ጨምሮ በሌሎችም የሳይንሱ ፋይዳ ባልተገለጸላቸው ታዳጊ አገራት በብዙዎች ዘንድ የህዋ ሳይንስ ለድሃ አገራት አያስፈልግም የሚል የተሳሳተ አመለካከት አለ። በዚህ ረገድ የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታት እንደ የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ እና የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የመሳሰሉ ተቋማት ለዓመታት ያደረጉት ጥረት ፍሬ ማፍራት የጀመረ ይመስላል። በአመለካከት ላይ ትኩረት ተደርጎ በመሠራቱ፤ እንዲሁም መንግሥትም ለጉዳዩ ትኩረት መስጠቱ ለዚህ ለውጥ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው።

በዚህም ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ታኅሣሥ 10 ቀን 2012 ዓ.ም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደጠፈር የመጠቀችው ETRSS-1 የኢትዮጵያ የመሬት ምልከታ ሳተላይት ከመጠቀችበት ጀምሮ ተልዕኮዋን በአግባቡ ማሳካት ችላለች። የተሰጣትን የመሬት ምልከታ ሥራዎችንም በአግባቡ አከናውናለች። ለሁለት ዓመት ተኩል እንደምታገለግል ተደርጎ የታቀደ ሲሆን፤ አሁን ላይ ከታቀደላት ጊዜ በላይ ተጨማሪ አምስት ወራትን አገልግላለች። በዚህም በግብርና፣ በተፈጥሮ ሀብት መስክና ከመሬት አስተዳደር ጋር የተገናኙ ሥራዎችን ለማከናወን ውጤታማ የሆኑ መረጃዎችን መስጠቷን የስፔስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጠው መረጃ ላይ ተመላክቷል።

ከዚህ በተጨማሪም የሳተላይቷን መረጃ በመጠቀም የለሙና አሁንም ሆነ በቀጣይ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ ሞዴሎች እንዳሉም ተጠቅሷል። በግብርናው ዘርፍ የሰብል ምርታማነትን በተመለከተ ከሳተላይቷ የተገኘውን መረጃ በመጠቀም ማልማት እንደተቻለም ተገልጿል። የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ማዕከል ያደረገ የደን ሽፋንና በጊዜው ውስጥ የሚኖረውን ለውጥ ለመከታተል የሚያስችል መተግበሪያም እንዲሁ ሳተላይቷ በሰጠችው መረጃ አማካኝነት ማልማት እንደተቻለም ተመላክቷል።

በየጊዜው ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጋር የተገናኙ መረጃዎችንም በግብዓትነት ለመጠቀም እንደተቻለ፤ በቱሪዝም ዘርፍ በተለይም በደቡብ ኦሞና በጋሞ ዞን የቱሪዝም ካርታ ለማዘጋጀትና ከዚህ ሥራ ጋር የሚገናኙ መተግበሪያዎችን የማበልጸግ ሥራዎችም በግብዓትነት ጥቅም ላይ መዋላቸውም ታውቋል። ከዚህም ባሻገር በኢትዮጵያ ውስጥ ለጥጥ እርሻ አመቺና ተስማሚ የሆኑ ቦታዎችን ለመለየት የETRSS-1 ሳተላይት መረጃ በግብዓትነት ማገልገሉም በመረጃው ተጠቅሷል። በሳተላይቷ አማካኝነት ለተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ለምርምር ሥራ የሚሆኑ መረጃዎችን የመስጠት ሥራዎችም ተከናውነዋል። መረጃውን ከመጠቀም አንጻር የተፈጠረው አቅም የተሳካ እንደነበርም ተገልጿል። ከዚህም ባሻገር የተፈጠረ የቴክኒክ አቅም መኖሩም ተመላክቷል። ታዲያ ከዚህ የበለጠ ለአገር ሁለንተናዊ ዕድገት የሚጠቅም ሥራ በሳተላይት ሳይንስ ካልሆነ በቀር ከወዴት ይገኛል?

ስለሆነም ከዚህ ድንቅ ሳይንስ በረከት ለመካፈልና ለአገር ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያበረክተውን ፈርጀ ብዙ ፋይዳ መሬት ላይ አውርዶ ለመጠቀም ሳይንሱ እንዳያድግ የዘርፉ የዘመናት ማነቆ ሆኖ የቆየውን «ምግብ ሳይጠገብ ምን የሚሉት የጠፈር ምርምር ነው» በሚል የተሳሳተ አመለካከት ሳይደናቀፉ ጅምሩን አጠናክሮ መቀጠል ከሁሉም በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ለማስታወስ እንወዳለን። ለዚህም ነው ከፖለቲካ ውጪ ሌሎች የፍልስፍናና የዕውቀት ዓይነቶች፣ ጥበቦችና ሳይንሶች ለማይታያቸውና አገር በፖለቲካ ብቻ የምትኖር ለሚመስላቸው ወገኖችም «አገር በፖለቲካ ብቻ አትኖርም፤ ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ በሚወጣ ኃይል ጭምር እንጂ» ልል የወደድኩት። ለዛሬው አበቃሁ፤ ሰላም!

# ማን እንደ «አገር በቀል ...» («ባህላዊ የፍትህ ስርአት» እንደ ማንፀሪያ)

ግርማ መንግሥቴ

በዛሬዋ ዘመን ዓለማችን በዴሞክራሲ፣ በሕግ የበላይነት፣ በሰብአዊ መብቶች ... ላይ አተኩሮ መሰራት የምርጫ ጉዳይ አይደለም። በዛሬው መልክ አይሁን እንጂ በድሮዋ ዓለምም፣ በጥንታዊቷ ምድርም ያውና ያው ሲሆን፤ በጠቀስናቸው ጉዳዮች ላይ መስራት የህልውና ጉዳይ ነው። እንደውም፣ አንዳንድ አንጋፋ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ከሆነ፣ በተጠቀሱትም ሆነ በሌሎች ሰብአዊ ጉዳዮች ላይ ከዛሬዋ ዓለማችን በተሻለ በጥንታዊቷ ዓለማችን ይሰራ ነበር። ለምሳሌ ያህል ሲጠቅሱም፣ የሰው ልጅ ሰብአዊ መብት ጥበቃ ከዛሬው ይልቅ በጥንቱ ዘመን ይሻል ነበር፤ ሰላም ከዛሬዋ ዓለም ይልቅ በጥንታዊቷ ዓለም ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የሰፈነ ነበር፤ የሰዎች የእርስ በርስ ተግባቦት ከዛሬዋ ይልቅ በጥንታዊቷ ዓለማችምን የሚያስቀና ነበር።

ዲሞክራሲ ማለት ሕዝባዊ አገዛዝ ማለት ከሆነ ከዛሬው ይልቅ የድሮው ሰብአዊ ነበር፤ እርቅና ሰላምን በተመለከተም ከዛሬዋ ዓለም ጋር በማይገናኝ ሁኔታ የጥንቱ እጅግ የላቀ ነበር፤ በሰላም ወጥቶ መግባትም፣ ወልዶ መሳምም ሆነ ዘርቶ መቃም ... ከዛሬዋ አለማችን ይልቅ በጥንቷ አለማችን ... ወዘተርፈ በማለት ይዘረዝራሉ። ዝርዝሩ (መተሳሰብ፣ መረዳዳት፣ መከባበር ...ን ጨምሮ) ብዙ ስለሆነ ወደ ተነሳንበት ርእሰ ጉዳያችን እንመለስ። በቅድሚያም፡-

"ሕግ እና ፍትህ በጥብቅ የተቆራኙ ቢሆንም የተለያዩ ጽንሰ-ሀሳቦች ናቸው። ሕግ "ይህንን አድርግ፤ ያንን አታድርግ" የሚል ድንጋጌ ነው። አቅም ያለው ሁሉ የፈለገውን ሕግ አውጥቶ ሊያስፈጽም ይችላል። ፍትህ ግን፣ ሰዎች ተሳስበው እና ተጋግዘው እንዲኖሩ የሚያደርግ፤ አድልዎንና ጥቃትን የሚከላከል፤ በዳይን የሚቀጣ፣ ተጠቂን የሚክስ በጎነት ነው። ፍትህ የማኅበራዊ ተቋማት ቀዳሚ በጎ ውጤት ነው። ሕግ መሣሪያ ሲሆን ፍትህ ደግሞ ሕጉ በተግባር ላይ ሲውል የሚገኘው ውጤት ነው። ጥሩ ሕግ በሥራ ላይ ከዋለ ፍትህን ያስገኛል። ጥሩ ሕግ ኖሮ ሥራ ላይ ካልዋለ ግን ሕጉ መኖሩ ብቻውን ፍትህን አያስገኝም። መጥፎ ሕግ ደግሞ ፍትህን ያጓድላል፤ ኢፍትሃዊነትን ያነግሳል።" የሚለውን የባለሙያዎች ብያኔ ለጠቅላላ እውቀትም ቢሆን እንያዘው። (በብያኔው ላይ ችግር ካለ መወያየት ይቻላል።)

በአንድ ወቅት ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ ያደረጉት አቶ ሰለሞን አረዳ (የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት) ‹‹በፍርድ ቤት ላይ እምነት ማጣት በመንግስት ላይ እምነት ማጣትን ያስከትላል፡፡ ያለ ጠንካራ ፍርድ ቤት ስለ ሀገር ግንባታ ማሰብ አይቻልም›› በማለት የሰጡትን አስተያየትም እዚሁ ላይ በደጋፊነት ማቅረብ ጉዳዩን ለማስረጽ ይረዳል፡፡ አቶ ሰለሞን በዚሁ ቃለ ምልልሳቸው ወቅት እንዳሉት "በሀገር ግንባታ ውስጥ "ሕገመንግስታዊነት፣ የሕግ የበላይነት፣ ስርዓት ያለው የመንግስት አወቃቀር፣ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ዋስትና የሚባሉት ነገሮች ሁሉ ያለ ዳኝነት አካሉ ሊታሰቡ አይችልም፡፡ ለዚህ ነው እንግዲህ የዳኝነት አካሉ ለዜጎችም ሆነ ለአንድ አገር የማይተካ ሚና ይጫወታል የምንለው፡፡" ያሉትን ከዚሁ ጋር በተያያዥ ጠቅሶና የጉዳዩን ውስብስብነት አቅልሎ ማለፍ ይቻላል።

### አሁን ደግሞ "አገር በቀል እውቀት"ንና መሰረታዊ ፋይዳውን በተመለከተ የጋራ መግባባት የተደረሰበት የሚመስለውን ሀሳብ እንመልከት።

"የአገር በቀል እውቀትንና ትምህርትን ፋይዳ በሚገባ በመረዳት ሞራልና ግብረገብነትን የተላበሰ ኅብረተሰብ መፍጠር እንደሚያስፈልግ፤ እስካሁን በአገሪቱ የተተገበሩት ሥርዓተ ትምህርቶች የአገሪቱን የኋላ ታሪክ ያላካተቱ፤ የወደፊት ጉዞዋን መሠረት ያላደረጉና ከምዕራባውያን የመጣውን በጭፍኑ የተቀበሉ ናቸው" የሚለው መቸም ያልሰለቸው (በተለይ የከተሜው ዜና ተከታታይ) የለም ማለት ይቻላል። ችግሩ የተግባር ጉዳይ እንጂ በአንደበት ተደጋግሞ የተነገረ ነው። ከዚህ ውስጥ "የአገሪቱ የኋላ

> **"ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ" ከሚለው ጀምሮ፣ የትም አገር ቢኬድ አገር በቀል እውቀት (IKን የሚተካከል መፍትሄም ሆነ አሰሪ መሳሪያ አይገኝም። ናይጄሪያ ከባህላዊ መድሀኒት ጀምሮ ትጠቀምበታለች። ሩዋንዳ ሳምን የሰላም፣ የብልፅግና፣ የግጭት ማስወገጃ የእናትነት ... ተምሳሌት በማድረግ የእለት ተእለት ስራዋን ታከናውናለች። ህንድ፣ ሩሲያ (የቻይናን አንስተን አንጨርሰውም ) እና ሌሎችም አገር በቀል እውቀታቸውን ለመድህናቸው ሲጠቀሙበት እንጂ የራሳቸውን ጥለው የሌላ ፍለጋ ሲኳትኑ አይታዩም**

ታሪክ ምን ይመስላል?" የሚለውን እንመልከት።

### አገር በቀል እውቀታችን ያለበት ይዞታ

እንደ የአንድሮሜዳ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጅ (ዶክተር ሮዳስ ታደሰ) ኢትዮጵያ በፍልስፍናው፣ በሥነ ፈለክ፣ በሕክምናውና በማዕድን ጥናት ዓለምን የሚያስደምሙ እውቀቶች ያላት አገር ብቻ ሳትሆን የስልጣኔዎች ሁሉ መነሻና ምንጭ ነች። በተለይ ምዕተ ዓመትን ሊደፍን ጥቂት ፈሪ የሆነውን፣ የጥቁር አሜሪካዊቷ ድሩሲላ ጁንዲን ስራዎች ያገላበጠ ይህንን እውነት አንድ፣ ሁለት .... በማለት ቆጥሮ መቀበል ይችላልና ስለ እውነትነቱ መከራከር የመከራከር ፍላጎትን ከማርካት ያለፈ ፋይዳ የለውም። ያ ማለት የእኛ የኋላ ታሪክ በሁለንተናዊ ይዞታው የበለፀገ ነበር ማለት ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና ትምህርት ክፍል መምህር ዶ/ር ጠና ደዎ እንደሚሉት ከሆነ "አሁን ካለው አኗኗራችን መረዳት እንደሚቻለው ማህበራዊ እሴቶቻችን እየተዳከሙና እየተሸረሸሩ መጥተዋል"። በመሆኑም ከዚህ አይነቱ ብርቱ ችግር በመውጣት "እሴቶቹ በአገሪቱ እየተወሰደ ያለውን የለውጥ እርምጃ ሊያግዙ በሚችሉበት መልኩ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው።እሴቶቹን ለማጠናከርም የአስተዳደራዊና ፖሊቲካዊ ርዕዮተ ዓለሞችን ከባዕድ አገሮች ከማምጣት ይልቅ የአገር በቀል ዕውቀቱን ከሳይንሱ ጋር በማስታረቅ ተስማሚውን መቅረፅ አስፈላጊ" ነው። "እየተሸረሸሩ የመጡትን አገራዊ እሴቶችን ለማበልፀግ በትምህርት ስርዓት ውስጥ አካቶ ማስተማር" ይገባል።

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የሥነ ትምህርት ፋካልቲ "አገር በቀል ዕውቀትና ትምህርት በኢትዮጵያ ፤ ፋይዳው፣ ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫው" (2011 ዓ.ም) በሚል ርዕስ ያዘጋጀው አገር አቀፍ ዐውደ ርእይ ላይም የተንፀባረቀው ይሄው መሆኑን ማስታወስና የዚህ ጽሑፍ አንባቢያንን ለተጨማሪ ንባብ መጋበዝም ተገቢ ይሆናል። በአውደ ርዕዩ ላይም "አገር በቀል ዕውቀትና ትምህርቱን በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ባለመካተቱ ፊደላዊና ከ'እኛ' ይልቅ 'እኔ' የሚል ማህበረሰብ ተፈጥሯል" የሚለው፤ እንዲሁም "የአገር በቀል እውቀትና ትምህርትን ፋይዳ በሚገባ በመረዳት ሞራልና ግብረገብነትን የተላበሰ ኅብረተሰብ መፍጠር" ይገባል የሚሉት ሀሳቦች በስፋት መንፀባረቃቸውንም ጠቆም ማድረግ ይገባልና አድርገነዋል።

እየተነጋገርን ያለነው፣ እየተነጋገርንብት ያለነው አገር በቀል እውቀት አካል የሆነውን፣ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓትን በተመለከተ ነውና ወደ'ዛው እናዝግም።

ከሚመለከተው ተቋም የተገኘውና ከርእሰ ጉዳያችን ጋር የሚሄደው መረጃ እንደሚያሳየው "የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት የፍትህ ሥርዓቱን ጠንካራ፣ ውጤታማና ብቁ ለማድረግ እና ኃላፊነትን በብቃት ለመወጣት እንዲቻል አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ የማሻሻያ እርምጃዎች እየወሰደ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህም አንጻር የፌዴራል የፍትሕና የሕግ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ከተሰጡት ዋና ዋና ተልዕኮዎችና ተግባራት አንዱ ችግር ፈቺ የፍትህና የሕግ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ ይህን ተልዕኮ ለመወጣት የኢንስቲትዩቱ የጥናትና ምርምር ዘርፍ ተደራጅቷል፡፡

በየዘርፉ ያሉ ነባር ሕጎችን ለማጠቃለል፣ ከወቅቱ የእድገት ደረጃ ጋር ለማጣጣም እና ለአጠቃቀም ምቹ ሆነው እንዲሻሻሉ ለማድረግ፤ የአገሪቱን የሕግ ሥርዓት ለማሟላት የሚያስችሉ አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት፤ የሕግ ትምህርት እና ሥልጠናን ለማጠናከር፤ የፍትህ አካላትን የሰው ሃብት ብቃት ለማሳደግ፣ አደረጃጀታቸውን እና አሰራራቸውን ለማሻሻል፤ እና ከሕግ ብዝሃነት ጋር የተያያዙ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች እና ሌሎች ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚረዱ ጥናቶችን ማካሄድ የዚህ ዘርፍ ተግባርና ኃላፊነት ነው፡፡" የሚል ሲሆን፤ "... ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ..." የሚለውን ከስሩ አስምረንበት ብናልፍ ተገቢ ይሆናል።

ዶ/ር ጠና እና ሌሎችም በዚሁ ሀሳብ በመስማማት "እሴቶቹን ለማጠናከርም የአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለሞችን ከባዕድ አገሮች ከማምጣት ይልቅ የአገር በቀል ዕውቀቱን ከሳይንሱ ጋር በማስታረቅ ተስማሚውን መቅረፅ አስፈላጊ" ነው ያሉትን ጉዳዩ ይሰምር ዘንድ እዚህ እንድገመው።

"በኅብረተሰቡ መካከል የነበሩ የመተሳሰብና አብሮ የመኖር ማህበራዊ እሴቶች በመሸርሸራቸውና በመዳከማቸው የችግር መፍቻ መሳሪያ በመሆን እያገለገሉ" አይደሉም። "በአገሪቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግጭቶችና አለመግባባቶች ተበራክተው በየክልሉ ዜጎችን ከቀዬአቸው እያፈናቀለ ያለውን ችግር ለመፍታት አገራዊ እሴቶቹ ጠቃሚ በመሆናቸው"ም ተገቢውን ትኩረት ማግኘትና በተግባር ላይ መዋል አለባቸው ነው የሚሉት ዶክተሩ።

"አገር በቀል እሴቶችን በማደራጀት ጥቅም ላይ ማዋል አለመቻሉ ጉዳት እንዳለው የገለጹት ዶ/ር ጠና፤ ከውጭ የሚመጡ እሴቶች ለአገሪቱ በሚሆን መልኩ ተቀምረው አለመወሰዳቸው ለተለያዩ ችግሮች መንስኤ" መሆናቸውንም ነው አስቀምጠው ያለፉት ።

ምን ማለት ነው፣ "የመረዳዳት፣ የመከባበር፣ አብሮ የመኖርና የመሳሰሉት አገር በቀል አቅማችን እየተዳከመ መምጣት የማህበራዊ እሴቶቻችን እየተዳከሙ እንጂ እየተጠናከሩ መምጣታቸውን አያሳዩም"። በመሆኑም፣ "ለአገር በቀል እሴቶች ተገቢውን ዋጋ መስጠት" የግድ ይሆናል እያልን ነው። ምሁራንም "በተለያየ የአገሪቷ አካባቢዎች ያሉ እሴቶችን በማጥናት ሁሉም የሚግባባበት እሴት ማጎልበት" አስፈላጊነት፤"ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚያግባባ እሴታዊ ስርዓት (ቫልዩ ሲስተም) ሊፈጠር" የሚገባ መሆኑን ነው ደጋግመው የሚመክሩት። ለዚህ ደግሞ "እሴቶችን የሚያጎለብት ተቋማዊ አደረጃጀት" ያስፈልጋል። ይህ ጸሐፊም በአዲስ ዘመን (ነሐሴ 20 /2014 ዓ.ም) ላይ"አገር በቀል እውቀት እና ወቅታዊ ይዞታው" በሚል ርዕስ ባሰፈረው ጽሑፍም ይህንን አረጋግጧል።

አቶ ሰለሞን አረዳ እንደሚሉት "የዳኝነት አካል በኢትዮጵያ ሥነመንግስት ረጅም ታሪክ አለው፡፡ በተለይም ደግሞ በዘመናዊ መንግስት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ወይም በንጉሥ ኃይለሥላሴ ዘመናዊ ሕጎች በኢትዮጵያ እንዲወጡ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ከአውሮፓ በመውሰድ ከአገር ሁኔታ ጋር እንዲዛመዱ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡" ያሉትንም ሆነ፣ አብዱልፈታ አብደላህ በ"የኢትዮጵያ የሀገር በቀል የአስተዳደር፣ የሕግና የፍትህ ሥርአቶች ማውጫ ቅጽ 1" (2010 ዓ.ም) መጽሐፋቸው ላይ "የሀገራችን የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር፣ የሕግና የፍትህ ሥርአት እስከ ሃየኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በሀገር በቀል እውቀቶችና እሴቶች የሚመራ እንደ ነበር አይዘነጋም።" በማለት በ"እንደ መግቢያ" ገፃቸው ላይ ያሰፈሩትን ወስደን ስንመለከት በርካታ ቁም ነገሮችን የምናገኝ ሲሆን፣ አንዱም በጉዳዩ ላይ ቀደምት የመሆናችን ጉዳይ፤ ቀጣዩ ደግሞ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ ስንገለገልበት የኖርነው በቀድሞው፣ በባህላዊው የፍትህ ስርአት ነበር ማለት ነው። በመሆኑም፣ የአገራችን ባህላዊ የፍትህ ስርአት ገና ለገና "ባህላዊ" ስለተባለ ብቻ አሽቀንጥረን ልንጥለው አይገባም እያሉን ነው።

አብዱልፈታ "አብዛኛዎቹ የሀገር፣ የሕዝብና የመንግሥት ችግሮቻችን መፍትሄዎች ከሀገር በቀል የአስተዳደር፣ የሕግና የፍትህ ሥርአቶቻችን ውስጥ መሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም።" ያሉትን፤ እንዲሁም፣ በዚሁ ስራቸው "ብዙዎቹ ምሁራኖቻችንና የመንግሥት መሪዎቻችን [ለችግሮቻችን] መፍትሄ ፍለጋና ለልምድ ልውውጥ አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ ሩቅ ምሥራቅና ሩሲያ የሚያንከራትቷቸው ጉዳዮች ሁሉ በእኛው የባህል እሴቶች ውስጥ መኖራቸውን ካወቅንና ከተገነዘብን ቆይቷል።" ሲሉ መታዘባቸውን ስንመለከት ርእሳችንን "ማን እንደ አገር በቀል ..." በማለት ማንነቱን መቀንበባችን ትክክል ሆኖ እናገኘዋለን።

"ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ" ከሚለው ጀምሮ፣ የትም አገር ቢኬድ አገር በቀል እውቀት (IK)ን የሚተካከል መፍትሄም ሆነ አሰሪ መሳሪያ አይገኝም። ናይጄሪያ ከባህላዊ መድሀኒት ጀምሮ ትጠቀምበታለች። ሩዋንዳ ላምን (ይህ አንዱ ምሳሌ ብቻ ነው) የሰላም፣ የብልፅግና፣ የግጭት ማስወገጃ፣ የእናትነት ... ተምሳሌት በማድረግ የእለት ተእለት ስራዋን ታከናውናለች። ህንድ፣ ሩሲያ (የቻይናን አንስተን አንጨርሰውም ) እና ሌሎችም አገር በቀል እውቀታቸውን ለመድህናቸው ሲጠቀሙበት እንጂ የራሳቸውን ጥለው የሌላ ፍለጋ ሲኳትኑ አይታዩም። እንግሊዝ (ከ'ኛ የወሰደችውን አስተርጉማ ነው የሚሉ አሉ) አገር በቀል ባህላዊ መድሀኒትን የሚያብራራ ዳጎስ ያለ መጽሐፍን አሳትማ ለሕዝቧ እነሆ ካለች አመታትን ያስቆጠረች መሆኑ ሌላው ለዚህ ጽሑፍ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው።

ባጠቃላይ፣ ያለ አገር በቀል እውቀትና ዘርፎቹ የትም አይደረስምና የሚመለከተው ሁሉ ለአፍታም ቸል ሊለው አይገባም እንላለን።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## እቁብን በቴክኖሎጂ

**አስናቀ ፀጋዬ**

እቁብ በኢትዮጵያ ባህላዊ የገንዘብ ቁጠባ መንገድ ሆና ለረጅም ዓመታት አገልግላለች። ይችን ባህላዊ የገንዘብ መቆጠቢያ መላ ጉራጌዎች እንደጀመሯትም ይነገራል። በዚች ባህላዊ የገንዘብ ቁጠባ ስልት ሰዎች ቡድን ፈጥረው በየወሩ ገንዘብ ሰብስበው በየተራ እየወሰዱ የገጠማቸውን የገንዘብ ችግር ፈትተዋል። አሁንም በዚቹ እቁብ አማካኝነት ሰዎች ንግድ ይጀምራሉ። የህክምና ወጪያቸውን ይሸፍናሉ። የሚያስፈልጓቸውን የቤት እቃዎችንም ያሟላሉ።

በኢትዮጵያ ባንኮች እየበዙ መጡ እንጂ የአብዛኛው ማህበረሰብ የገንዘብ ቁጠባ መንገድ እቁብ ነበር። አሁንም ቢሆን በተለይ የገጠሩ ህብረተሰብ ሁነኛ የገንዘብ ቁጠባ ዘዴ እቁብ ነው። ከነተረቱም ‹‹ሰውን ሰው ያደረገው እቁብ ነው›› ይባላል። ይህም እቁብ በማህበረሰቡ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነት ያለው መሆኑንና በድንገት ከሚያጋጥም ችግር መውጫያ መንገድ መሆኑን ያሳያል።

እስካሁን ድረስ እቁብ ባህላዊ መንገዷን ጠብቃ እዚህ የደረሰች ቢሆንም ታዲያ አሁን ላይ ግን በጥቂቱም ቢሆን ደረጃዋ ከፍ ያለ ይመስላል። ዘመናዊነትንም ተላብሳ ብቅ ብላለች። እንዴት? ያሉ እንደሆነ እቁቧን ለማዘመንና ደረጃዋንም ከፍ ለማድረግ በጋራ እየሰሩ ያሉ ወጣቶች ለዚህ ምላሽ አለን ይላሉ።


ወጣት አቤኔዘር እንግዳ ‹‹ውጆ›› የተሰኘና የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ላይ የሚሰራ መተግበሪያ ከፈጠሩ ወጣቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን የዚሁ ቴክኖሎጂ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ያገለግላል።

እርሱ እንደሚለው ‹‹ውጆ›› በጉራጌኛ ቋንቋ እቁብ ማለት ሲሆን የቴክኖሎጂ ድርጅቱ ስም የፈለቀውም ከዚሁ የጉራጌኛ ቃል ነው። በቀደመው ታሪክ እቁብ ሸቀጥ ላይ ያተኮረና ሰዎች ግብይት የሚያካሂዱት እቃን በእቃ በመለዋወጥ ነበር። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በሀገሪቱ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበትና አሉታዊ የኢኮኖሚ ተፅእኖ ይታያል። እቁብም በባህሪው ለእቁብተኛው በግዜ ገደብ ገንዘብ የሚደርሰው በመሆኑ መጀመሪያና መጨረሻ ገንዘቡ ሲወሰድ እኩል ዋጋ ሊኖረው አይችልም። በዚህ መነሻነት አንድ ሰው የወጣለትን እቁብ ለምን ወደሸመታነት አይቀይረውም በሚል በውስጡ የኢ ኮሜርስ ፓላትፎርም በማጣቃለል የሚሰራ ‹‹ውጆ›› የተሰኘ መተግበሪያ በለፀገ።

የትምህርት እድል አግኝቶ በቻይና ሀገር እንደነበር የሚያስታውሰው ወጣት አቤኔዘር፤ እዛ በነበረው ቆይታ ‹‹ዊ ቻት›› የተባለ መተግበሪያ ማየቱንና በዚሁ መተግበሪያ አማካኝነት ሁሉንም የፋይናንስ ጉዳዮች በአንድ ላይ በማድረግ ሲጠቀሙበት መታዘቡን ያስረዳል። ይህንኑ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ በሀገር በቀል ሀሳብ ለምን ወደ ኢትዮጵያ አናመጣውም በማለት ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ ስራውን እንዳስጀመረም ይናገራል።

እንደ ወጣት አቤኔዘር ገለፃ በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ነው የተባለለት ይህ የፋይናንስ መተግበሪያ በውስጡ ሰዎች እቁብ እንዲጥሉ፣ ብድር እንዲያገኙና ሸመታ እንዲፈፅሙ ያስችላል።

በዚሁ መተግበሪያ አማካኝነት ሁለት ስራዎች የሚከናወኑ ሲሆን በመጀመሪያው ከቢዝነስ ድርጅቶች ጋር በመጣመር ለድርጅት ሰራተኞች እቁብ እንዲቀርብ ይደረጋል። በሁለተኛው ደግሞ ግለሰቦች፣ የቤተሰብ አባላትና ሌሎችም የህብረተሰብ



ወጣት አቤኔዘር እንግዳ፤

ፎቶ፡- በአስናቀ ፀጋዬ

ክፍሎች እቁብ የመጀመር ሃሳብ ካላቸው ሶስትና አራት ሆነው ሲመጡ ከመካከላቸው አንዱ ለድርጅቱ እንደ ወኪል ሆኖ ያገለግላል። በዚህም ድርጅቱ ከሚያገኘው ሶስት ከመቶ የአገልግሎት ክፍያ እኩል ተካፍሎ ጥቅሙን እያገኘ ኃላፊነት ወስዶ የማህበረሰቡን እቁብ እንዲያሳልጥ ያደርጋል።

‹‹የእቁብ አሰባሰቡ ዲጂታል እንዲሆን በማሰብም ጭምር ነው መተግበራዊ የበለፀገው›› የሚለው ወጣት አቤነዘር እቁብ በባህሪው የተለያዩ እጥረቶች የሚታዩበት መሆኑን ይገልፃል። እቁብ በቀላሉ ተደራሽ አለመሆኑ፣ አቅምን ያገናዘበ፣ በሰአቱ ሊደርስ የማይችልና ትክክለኛነቱም አጠያያቂ መሆኑ ከእጥረቶቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውንም ያብራራል።

እነዚህኑ እጥረቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት እቁብ ዲጂታላይዝድ ቢደረግ እጥረቶችን በመፍታት ረገድና ስራውንም በማቀላጠፍ በኩል ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ከሚል እሳቤ በመነሳት እርሱና ጓደኞቹ ስራውን እንደጀመሩት ያስረዳል።

የሀገሪቱ የፋይናንስ ሴክተርም ይህን ጉዳይ ቸል ያለው በመሆኑና በተለይ ደግሞ የጥቃቅንና አነስተኛ የቁጠባና ብድር ተቋማት በዲጂታል መንገድ ብድር ገና በቅርቡ የጀመሩ በመሆናቸው በዚህ ረገድ የሚታየውን ክፍተት ከመፍታት አኳያ የመተግበሪያው ሚና የጎላ መሆኑንም ይጠቅሳል።

ወደ 44 ከመቶ የሚሆነው የሀገሪቱ ህብረተሰብ ከዝቅተኛ እስከመካከለኛ ገቢ ያገኛል የሚል መረጃ በመኖሩ ለነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች መተግበሪያው አማራጭ የፋይናነስ አገልግሎት ሆኖ እንደሚያገለግል ወጣት አቤኔዘር ይጠቁማል።

የገንዘብ ንክኪውንም ከመቀነስ አኳያ የመትግበሪያው ሚና የጎላ መሆኑንም ጠቅሶ፤ ድርጅቱ ፕላትፎርሙን በድረገፅና በመተግበሪያ በማቅረብ ገንዘቡ በባንክ በኩል ለተጠቃሚው እንዲቀርብ የሚደረግ መሆኑንም ያስረዳል። የድርጅቱ ተግባር እቁቡን ማስተዳደር ብቻ መሆኑንም ነው የሚጠቁመው። መተግበሪያውን ያላወረደ ሰው ካለም በድረገፁ አማካኝነት እንዲጠቀም የሚያስችለው መሆኑንም ይገልፃል።

ወጣት አቤኔዘር እንደሚለው በአሁኑ ግዜ ድርጅቱ ከተለያዩ የቢዝነስ ድርጅቶች ጋር ስምምነት በመፍጠር ሰራተኞች በሚፈልጉት አማራጭ በመተግበሪያው በተጋጀላቸው ጥቅል አማካኝነት ከደሞዛቸው ውጪ አማራጭ የቁጠባ እቅድ እንዲኖራቸው እየሰራ ይገኛል። ከቢዝነስ ድርጅቶች ውጪ ያሉ ሌሎች ሰራተኞችም ከመካከላቸው አንዳቸው ወኪል ሆነው ይመዘገቡና ድርጅቱ ከሚያገኘው የአገልግሎት ክፍያ ተጠቃሚ እንዲሆኑና እቁቡን በማሳለጥ ረገድ ሃላፊነት እንዲወስዱ ይደረጋል።

የቴሌኮምና የኢንተርኔት መሰረተ ልማት እምብዛም ባልተስፋፋበትና የህብረተሰቡም የዲጂታል እውቀት እምብዛም ባለሆነበት በዚህ ጊዜ ባህላዊ የገንዘብ ቁጠባ መንገድ የሆነውን እቁብ በዲጂታል መንገድ ማሳለጥ የራሱ የሆነ ተፅእኖ አለው። ይሁንና ድርጅቱ እንዲህ አይነቱ ችግር በሂደት የሚፈታና የሚቀየር መሆኑን በማመን ስራውን እያከናወነ ይገኛል።

በተለይ የህብረተሰቡ የዲጂታል እውቀት ገና ያላደገ እንደመሆኑ የዲጂታል ግንዛቤን በህብረተሰቡ በማስፋትና አሁን እያደገ የመጣውን የዲጂታል መሰረተ ልማት እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም እቁብን ጨምሮ ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ የፋይናስ ስራት ለማስፋት ጥረት ይደረጋል። በተለይ ኢትዮ ቴሌኮም ለግል ባለሃብቶች በሩን ክፍት በማድረጉና ይህንኑ ተከትሎ መሰረተ ልማቱ የመስፋት እድሎች ስለሚኖሩ ውጣውረዱን መቋቋምና አገልግሎቱን ለህብረተሰቡ ማቅረብ ይቻላል።

በአሁኑ ጊዜም ድርጅቱ ቀስ በቀስ እድገትና መሻሻሎች እያሳየ መጥቷል። ለጊዜውም ከ ‹‹ቻፓ›› እና ከ ‹‹ቴሌ ብር›› ጋር በመሆን እየሰራ ይገኛል። በሂደት ደግሞ እቁብን በቴክኖሎጂ የማሳለጥ ተግባር በሀገር ደረጃ መለያ እንዲሆን በማድረግ በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ወደ ኬኒያ፣ ሩዋንዳና ጂቡቲ ጭምር እንዲሰፋ የማድረግ ውጥን አለ።

ጥናቶችም እቁብን ጨምሮ ፋይናስን በቴክኖሎጂ የማሳለጥ ተግባር በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ተግበራዊ እየሆነ እንደሚገኝ ያሳያሉ። ሙሉ ስያሜውም /Rotating Saving And Credit Association/ ተብሎ ይጠራል። ከዚህ አንፃር ይህን ቴክኖሎጂ መለያ በማድረግ በኢትዮጵያ መስራት ከተቻለ በአህጉርና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚሰፋበት እድል አለ። የማህበረሰቡ የዲጂታል እውቀትም በጊዜ ሂደት እየተሻሻለ ይመጣል ተብሎ ይታሰባል።

እቁብን በዲጂታል ቴክኖሎጂ የማሳለጡ ተግባር በአሁኑ ጊዜ በሙከራ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚናገረው ወጣት አቤኔዘር፤ በቀጣይ እ.ኤ.አ በ2023 አዲስ አመት ሙሉ በሙሉ ወደትግበራ እንደሚገባ ይጠቁማል። ከዛ በፊት ባሉት ጥቂት ወራት ግን እቁብን መሰብሰብና ከአገልግሎት ክፍያ ገቢ ማግኘት ብቻ ሳይሆን አጋር አካላትን በማሰባሰብ እቁቡ እስኪያልቅ ድረስ ደምበኞች ሸመታ እንዲፈፅሙ በማሰብ ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙም ያመላክታል።

ለአብነትም ድርጅቱ ፈሬሽ ኮርነር፣ ብላክ ፐርፐዝ ኢትዮጵያና ሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር በአጋርነት እየሰራ እንደሚገኝ ይጠቅሳል። ወደፊት ደግሞ ደንበኞች እቁብ በመጣል እንደ አስቤዛና የቤት እቃዎችን የመሰሉ መሰረታዊ ሸመታዎችን በመተግበሪያው አማካኝነት እንዲከውኑ የማድረግ ውጥን መያዙንም ወጣት አቤኔዘር ይጠቁማል። በአሁኑ ጊዜ ግን እርሱና ጓደኞቹ እቁቧን ብቻ በማስጣል ቴክኖሎጂው ያስኬዳል ወይስ አያስኬድም የሚለውን የመሞከር ሂደት ላይ እንደሚገኙም ነው የሚጠቅሰው።

ቴክኖሎጂ ችግር መፍቺያ መሳሪያ ከሆነ ሰነባብቷል። የሰዎች ህይወትና የአኗኗር ዘይቤም በቴክኖሎጂ እየቀለለ መጥቷል። የሰዎችን የአኗኗር ሁኔታ ከማሻሻል በዘለለ ቴክኖሎጂ የሀገርን ኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድም ቁልፍ ሚና እየተጫወተ መጥቷል። መንግስትም በቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት በማድረግና በጀት በመመደብ የዜጎችን ህይወት ለማሻሻልና የሀገርን ኢኮኖሚም ለማሳደግ ብርቱ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ለዚህም ቴክኖሎጂውን የሚመራና የሚቆጣጠር ተቋም ከመገንባት ጀምሮ ሌሎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራን የሚያግዙ ተቋማትን አቋቁሞ ስራዎች እያከናወነ ይገኛል። በዚህ ረገድ ደግሞ ወጣቶች በቴክኖሎጂ ላይ አተኩረው በመስራት ራሳቸውንና ሀገራቸውን እንደሚጠቅሙ ይጠበቃል።

ወጣት አቤኔዘርና ጓደኞቹ ሀገር በቀል የገንዘብ ቁጠባ መንገድ ከሆነው እቁብ በመነሳት በቴክኖሎጂ ተደግፎ እንዲሰራ እያደረጉ ያሉት ጥረትም ለዚህ ጥሩ ማሳያ በመሆኑ ሊበረታታና ሊደገፍ ይገባል። መንግስትም መሰል ተግባራትን ለመፈፀም ዝግጁ ለሆኑ ወጣቶች ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

እኛም ወጣት አቤኔዘርና ጓደኞቹ ቴክኖሎጂን መሰረት አድርገው እቁብ ላይ እየሰሩ ያሉትን ተግባር በማድነቅ በቀጣይ ስራቸው መሬት ላይ ወርዶ ከራሳቸው አልፎ በርካቶችን ሊጠቅም እንደሚችል ተስፋ እናደርጋለን። ሌሎች ወጣቶችም በእነርሱ ስራ ተነሳስተው ቴክኖሎጂን በመጠቀም ችግር ፈቺ ስራዎችን ይሰራሉ ብለን እናምናለን። በዚህም ከራሳቸው አልፈው ሀገራቸውንም እንደሚጠቅሙ ይታሰባል።

**ሰላም!!**

# የወርቅ ማዕድን ልማትና ሜድሮክ ኩባንያ

**ስምስም መንግሥቱ**

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ በግብርናው ዘርፍ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ላቅ ያለ ድርሻ እየተወጣ ያለው ቡና አረንጓዴው ወርቅ እስከ መባል ደርሷል። ከምድር በታች ከሚገኙት የማዕድን ሀብቶች መካከል ደግሞ የወርቅ ማዕድን ይጠቀሳል። ኢትዮጵያ ክፍለ ኢኮኖሚውን ከፍ ሊያደርግ የሚችል የምድር በረከት ያላት አገር ስለመሆኗም አብዝቶ ይነገራል። በኦሮሚያ ክልል እንደ ጉጂ ዞን፣ በቤኒሻንጉልጉሙዝ ክልል ደግሞ ከማሺ፣ መተከልና አሶሳ ያሉ አካባቢዎች በወርቅ ሀብት ክምችታቸው በቀዳሚነት ቢጠቀሱም በመላው የአገሪቱ አካባቢዎች የወርቅ ማዕድን ሀብት እንደሚገኝ መረጃዎች ይጠቁማሉ።በኢትዮጵያ የወርቅ ማዕድን በቁፋሮ ከመሬት ውስጥ በማውጣት ጥቅም ላይ ማዋል ረጅም አመት ያስቆጠረ ስለመሆኑም የታሪክ ድርሳናት ምስክር ናቸው። መንግሥትም ለማዕድን ኢንዱስትሪው ልማት ትኩረት ሰጥቶ እንደሚንቀሳቀስ ይታወቃል፡፡

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ከቡና ቀጥሎ ትልቅ ተስፋን ያሳደረው የወርቅ ማዕድን እጅግ ኋላቀር በሆነ የአመራረት ዘዴ መከናወኑ በኢኮኖሚው ላይ የሚፈለገውን ያህል ድርሻ እንዳይኖረው እንዳደረገው እንደ አንድ ምክንያት ይጠቀሳል። ዛሬም ድረስ የወርቅ ማዕድን ልማት የሚታቀደው ባህላዊ የወርቅ አምራቾችን መሠረት በማድረግ ነው። ለአብነትም በቤኒሻንጉልጉሙዝ ክልል በ2014 በጀት አመት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተመረተውን የወርቅ ማዕድን በተመለከተ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት በዘገባው ያመለከተውን መጥቀስ ይቻላል። እንደዘገባው ክልሉ በባህላዊ አምራቾች አማካኝነት 20 ኩንታል ወርቅ ለማምረት አቅዶ የተመረተው ግማሹ ነው። ግማሹም የተመረተው በክልሉ አምራች ከሆኑት ሦስት ዞኖች መካከል በአንዱ ብቻ ነው። ለአፈጻፀሙ ዝቅተኛ መሆን በምክንያት የተጠቀሰው በክልሉ ያጋጠመው የፀጥታ መደፍረስ ነው፡፡

በባህላዊ የወርቅ አምራቾች ላይ መሠረት ያደረገ እንቅስቃሴ ደግሞ ዘርፈብዙ ክፍተቶች እንዳሉበት ይነገራል። ባህላዊ ወርቅ አምራቾች በግንዛቤ ማነስና በተለያየ ምክንያት ያመረቱትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ በማቅረብ እራሳቸውንም አገርንም ተጠቃሚ ከማድረግ ይልቅ በመኖሪያቤታቸው ውስጥ የማስቀመጥ አዝማሚያ እንደሚስተዋልባቸው፣ ለገበያ አቅርበው ከሚያገኙት ገቢ ቆጥበው ኑሮአቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉት ጥረት አናሳ መሆን፣ በዘርፉ ላይ ለሚገኘውም የኑሮ ለውጥ ያላስገኘ ዘርፍ ሆኖ እንዲታይ ማድረጉን፣ ባህላዊውን የአመራረት ዘዴ መሠረት በማድረግ ባልደከሙበት ሥራ በአቋራጭ ለመክበር የሚንቀሳቀሱ ሕገወጦችን ማበራከቱ ተደጋግሞ የሚነሳ ጉዳይ ነው። በዚህ ተግዳሮት ውስጥ የሚገኘውን ወርቅ የማምረት ዘዴ በዘመናዊ አሠራር መተካት ግድ ነው። በተለያየ ዘርፍ መጠነሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ በራስ አቅም የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ጥረት በሚደረግበት በዚህ ወቅት የማዕድን ልማቱን በማዘመን ከዘርፉ የሚገኝ ገቢን ለማሳደግ በመንግሥት በኩል የሚቻለው እየተደረገ ይገኛል።በወርቅ ማዕድን ልማት የገንዘብ አቅም፣ ቴክኖሎጂ፣ እውቀትና ክህሎት ያላቸውን የውጭና የአገር ውስጥ ኩባንያዎች ለመሳብም በተለያየ አማራጭ መንግሥት ጥረቱን አጠናክሮ ቀጥሏል።እንቅስቃሴው ተጠናክሮ ከቀጠለ በአጭር ጊዜ ለውጦችን ማምጣት እንደሚቻልም እየተገለጸ ነው፡፡

እንዲህ እየተደረገ ባለው ጥረት በግሉ ዘርፍ በተሻለ ቴክኖሎጂና የገንዘብ አቅም በወርቅ ማዕድን ልማት ተሰማርቶ በአገር የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችል ኩባንያም መፍጠር ተችሏል። ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ይጠቀሳል። ኩባንያው የወርቅ ልማቱን እያከናወነ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን ኦዶሻኪሶ ወረዳ ለገደንቢ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው።ኩባንያው ቀድሞ በመንግሥት ይዞታ ሥር የነበረውን ድርጅት ነው የተረከበው። ኩባንያው ከመንግሥት ተረክቦ ወደ ሥራው ከገባ ጊዜ ጀምሮ በመልካምና በተግዳሮት ውስጥ ሆኖ በሥራው ይገኛል፡፡



**አቶ ቱሉ ስማ**

ኩባንያው በማዕድን ልማቱ ውስጥ ስላለው ቆይታ፣ በቆይታው ለአገር ያበረከተውን አስተዋጽኦ፣ የወደፊቱንም በተመለከተ ከሜድሮክ ወርቅ ኩባንያ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ከአቶ ቱሉ ለማ ጋር ቆይታ አድርገናል። አቶ ቱሉ እንዳሉት እንደ ሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በማዕድን ዘርፍ አንድ ዘርፍ በኩባንያው ውስጥ የተዋቀረ ሲሆን፣ በዚህ ዘርፍ ውስጥ ከተደራጁት መካከል ሜድሮክ ወርቅ አንዱ ነው። ተዛማች ማዕድናትም በዚሁ ክፍል ውስጥ ይከናወናል። ወርቅና ብር ከዋና ተግባራቱ መካከል ይጠቀሳል። የወርቅ ልማቱን በዋናነት የሚያከናውነው ኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን ኦዶ ሻኪሶ ወረዳ ውስጥ ቢሆንም፣ ቤኒሻንጉልጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ቡለን ወረዳ ውስጥ በከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ ባከናወነው የወርቅ ፍለጋ ጥናት በአካባቢው ልማት ማከናወን አዋጭ መሆኑን አረጋግጧል።ወደ ምርት ሥራ ለመግባትም የፋብሪካ ተከላ ለማከናወን በጨረታ ሂደት ላይ ይገኛል።ሂደቱ እንደተጠናቀቀም የፋብሪካ ተከላውን ማከናወንና አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን አሟልቶ ወደ ሥራ ለመግባት ኩባንያው ዝግጁ ነው።ባለፉት ጊዜያቶች በአካባቢው አጋጥሞ የነበረው የፀጥታ መደፍረስ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ባለመሆኑ ኩባንያው በሚያደርገው እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ ፈጥሯል።አሁን ላይ የፀጥታው መደፍረስ እየተሻሻለ በመሆኑ በዚሁ ከቀጠለ ወይንም ዘላቂነት ካለው ኩባንያው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ላይ የሚያከናውነው የወርቅ ማዕድን ልማት ሁለተኛው ፕሮጀክቱ ይሆናል።ኩባንያው በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተመሳሳይ የወርቅ ፍለጋ ጥናት በማካሄድ ላይ ሲሆን፣ ተስፋ ሰጪ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፋ ባለ የወርቅ ልማት ላይ በመሰማራት ኩባንያው ቀዳሚ ነው።በእስካሁኑ እንቅስቃሴውም በወርቅ ልማት በአገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ ካበረከተው አስተዋጽኦ በተጨማሪ ልማቱን በሚያከናውንበት አካባቢ ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣትና ሰፊ ቁጥር ላለው የሰው ኃይል የሥራ ዕድል በመፍጠር ድርሻውን ተወጥቷል፡፡

ኩባንያው በቴክኖሎጂ አጠቃቀሙ የሚገለጽበትንም አቶ ቱሉ እንዳስረዱት፤ ዓለም አቀፍ የአሠራር ሥርዓቶችን ዘርግቶ ደረጃውን በጠበቀ የልማት ሥራ በማከናወን በተመሳሳይ ልማት ላይ ከተሰማሩ ኩባንያዎች ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችለውን ተግባራት ነው በማከናወን ላይ የሚገኘው።የበለጠ ውጤታማ ለመሆንም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ጥረት ያደርጋል።አዳዲስ ፕሮጀክቶችንም በመቅረጽ ሥራዎቹን ለማስፋትም እየሠራ ነው።እራሱን ከማሳደግ ባሻገርም አነስተኛ አምራቾችንም ሆነ ባህላዊ አልሚዎችን አቅም በማሳደግ ልምዱን በማካፈል ያበረከተው አስተዋጽኦም ይኖር እንደሆን ለቀረበላቸው ጥያቄ አቶ ቱሉ ‹‹ኩባንያችን ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ወርቅ አልሚዎች ሞዴል ነው ማለት እችላለሁ።ባለሙያዎቻቸውን ለአቅም ግንባታ በመላክ፣ የሚፈልጉትን መረጃ በመውሰድና የአሠራር ሥርዓቶችን በማየት የሚወስዱት ነገር እንዳለ ሆኖ ጥያቄ ሲኖራቸውም የድጋፍ ምላሽ በመስጠት ትብብር ያደርግላቸዋል። በዚህ ረገድ የሚጠበቅበትን እያደረገ ወይንም እየተወጣ ነው።ወደፊት ግን የበለጠ በማገዝ ኃላፊነቱን ይወጣል›› በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።ለወርቅ ልማቱ የሚያግዝ የተሻለ ቴክኖሎጂ ያለው በመሆኑም የማሽን እገዛ እያደረገ አነስተኛ አምራቾችን እየደገፈ መሆኑን፣ በወርቅ ልማት ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ደግሞ አዳዲስ ኩባንያዎች የሚጠቅም የጥናት ሥራ አዘጋጅቶ በማቅረብ አገርን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሥራ እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ሁሉ የቴክኖሎጂና የገንዘብ አቅም ይዘው በወርቅ ማዕድን ልማቱ ለመሰማራት ማዕድኑ በሚገኝባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች የልማት ቦታ ወስደው ነገር ግን ወደ ሥራ ሳይገቡ ጊዜያቶችን ያስቆጠሩና አጥረው የያዙት ቦታም ለልማት ሳይውል መባከኑን በቅሬታ ይቀርባል።በዚህ ረገድ ቤኒሻንጉልጉሙዝ ክልል ይጠቀሳል።ክልሉ የልማት ቦታ አጥረው ረዘም ያለ ጊዜ አስቆጥረዋል ብሎ ካነሳቸው ኩባንያዎች መካከል ሜድሮክ አንዱ ነው።አቶ ቱሉ በዚህ ላይ ያላቸውን ምላሽ ጠይቀናቸዋል፡፡

እንደ አቶ ቱሉ ማብራሪያ እንደ ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያና ማይኒንግ ክላስተር የተነሳው ቅሬታ አይመለከተውም።ኩባንያው የልማት ቦታ ወስዶ ያላለማው የለም። በቤኒሻንጉልጉሙዝ ክልል ውስጥ በጥናት ሥራ ላይ ነው የቆየው። የጥናት ሥራ ሰፊ ስፍራን ያካልላል።ከብዙ ጥረት በኋላ ነው አነስተኛ በሆነ ሥፍራ ላይ ልማቱ የሚከናወነው።በተለያየ የጥናት ዘዴና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በተከናወነው የጥናት ሥራ ወደ 40ሺ ኪሎሜትር ሥፍራ ነው የተሸፈነው።በዚህ የቁፋሮ ሂደት ማዕድኑ ከተገኘ በኋላ በቤተሙከራ ውስጥ ምርምር ይከናወናል።የቤተሙከራውን ውጤት መሠረት በማድረግ ደግሞ ትንታኔ ይደረጋል።ይህ ሁሉ ሂደት የክምችት መጠኑን ለማወቅ፣ ክምችቱ ከታወቀ በኋላ ደግሞ ፋብሪካ አቋቁሞ፣ የሰው ኃይል ቅጥር ፈጽሞና መሠረተልማት አሟልቶ ልማቱን ማከናወን ለኩባንያውም ሆነ ለአገር ገቢ በማስገኘት ረገድ አዋጭ ስለመሆኑ በትንታኔው ይታያል። እንዲህ በጥናት ለይቶ ውጤት ላይ ለመድረስ ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል። ኩባንያው የረጅም ጊዜ ጥናቱን አጠናቅቆ ለፋብሪካ ተከላ ሥራ የጨረታ ሂደትን ለመወጣት በእንቅስቃሴ ላይ ሆኖ በክልሉ የፀጥታ መደፍረስ አጋጠመ። ይሄም ጊዜ እንዲወስድና እንዲራዘም አድርጎታል። ኩባንያው ለፋብሪካ ተከላና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማሟላት ድጋሚ ጨረታ ለማውጣት ተገድዷል። መዘግየቱ የተፈጠረው በምክንያት ነው። የፀጥታው ሁኔታ አስተማማኝ ከሆነ ኩባንያው ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጁ ነው። አሁንም በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡

ኩባንያው በሥራ ቆይታው በተግዳሮት የሚያነሳቸውና በጥንካሬም የሚገልጻቸው ነገሮች ካሉ እንዲገልጹልን አቶ ቱሉ ላቀረብንላቸው ጥያቄም በሰጡት ምላሽ፤ የወርቅ ልማት ሥራ ከከተማ ራቅ ባለ ፈታኝ የሆነ ነገር በሚያጋጥምበት ሥፍራ ነው የሚከናወነው። በተለይ ደግሞ የፀጥታ መደፍረስ ሥራን የሚያስተጓጉልና የደህንነት ሥጋት ስለሚፈጥር የበለጠ ፈታኝ ያደርገዋል። ከፀጥታ ጋር አገራዊ ችግር ሲያጋጥም የኩባንያዎች ሥራም ይጎዳል። እንዲህ ያሉ ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ በሥራው ውስጥ መቆየቱ፣ አሁንም ለተሻለ ውጤት ለመንቀሳቀስ ጥረት መደረጉና የመላው ሠራተኛና የኩባንያው የሥራ ተነሳሽነት በጥንካሬ ይገለጻል፡፡

ኩባንያው ልማቱን በሚያከናውንበት ሥፍራም ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያይዞ በአንድ ወቅት ላይ ስለተነሳበትም ጉዳይ አቶ ቱሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ ‹‹ለገደቢ ላይ ነው የተነሳው። በውጭና በአገር ውስጥ የሚመለከታቸው አካላት የተሳተፉበት ዝርዝር ጥናት በማካሄድ በተገኘው ውጤት ኩባንያው መጠነኛ የሆነ ማስተካከያ እንዲያደርግ ከማመላከቱ በስተቀር በጥናት ውጤቱ ኩባንያው ዓለም አቀፍ አሠራርን ወይንም ደረጃን ተከትሎ ልማቱን በማከናወን ላይ ይገኛል።መጠነኛ የሆኑትን ችግሮቹንም አስተካክሎ የምርት ሥራውን ቀጥሏል።ችግሮቹም እንደመጠጥ ውሃ የመሳሰሉ ለአካባቢ ማኅበረሰብ የመሠረተልማት ማሟላት ስለነበር ይህንንም እየፈጸመ ነው።ኩባንያቸው ዓለም አቀፍ አሠራርን በተከተለና አካባቢን በመጠበቅ አገርንና ድርጅቱን የሚጠቅም ውጤታማ ሥራ በመሥራት ኃላፊነት መወጣት የኩባንያው ራዕይ እንደሆነም አቶ ቱሉ በቆይታችን ገልጸውልናል።ኩባንያቸው በ2014 በጀት አመት ካመረተው ወርቅ የትርፍ ግብር ብቻ 910ሚሊዮን ብር መክፈሉን ጠቅሰዋል።

ኩባንያው በቅርቡ በሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደው የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ላይ ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲሁም ተሞክሯቸውን ይዘው ከቀረቡት መካከል አንዱ ነበር። ተሳትፎውን በተመለከተም አቶ ቱሉ እንዳስረዱት፤ ኩባንያቸው በወርቅ ማዕድን ልማት ካለው የረጅም ጊዜ ተሞክሮ እያከናወነ ስላለው ሥራና አስተዋጽኦውን በተመለከተ በማስተዋወቅ መንግሥት፣ ማህበረሰቡና ከሌላው ዓለምም የተገኘው ግንዛቤ እንዲኖረው ማስቻል ከኤክስፖው የተገኘው አንዱ ተሞክሮ ነው።በሌላ በኩልም ከፋይናንስ ተቋማት፣ ለዘርፉ ሥራ የሚያግዝ ቴክኖሎጂ ከሚያቀርቡት ጋር ግንኙነት መፍጠር መቻሉ ለቀጣይ የተሻለ ልማት ያግዛል። በአገር ውስጥ እንዲህ ያለ ኤክስፖ መካሄዱ ያነቃቃል። ሥራን የበለጠ ለማሳደግም ይረዳል። ከአገር ውጪ በካናዳ ደቡብ አፍሪካና በሌሎችም አገሮች የማዕድን ኤክስፖ ላይ ኩባንያው በመሳተፍ እራሱን ከማስተዋወቅ በተጨማሪ የሚጠቅሙትን የሌሎችን ተሞክሮና ልምዶች ይወስዳል። በተለይም ዘመናዊ የመሥሪያ ቴክኖሎጂና በሥራ ላይ ላሉት መሣሪያዎች መለዋወጫዎችን፣ እንዲሁም ለባለሙያ የአቅም ግንባታ ለማግኘት፣ ልማቱ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተዛምዶ እንዲከናወን የሌሎችን ተሞክሮ ለመቅሰም ኤክስፖዎችን እንደመልካም አጋጣሚ ይጠቀምባቸዋል። በዚህ መልኩ በመንቀሳቀስ ድርጅቱ የበለጠ እንዲያድግ እየተሠራ መሆኑን ነው አቶ ቱሉ ያስረዱት።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## መኖር ባይኖር

**በትረ ሙሴ (መልከ ሊትዮጵ)**

አስባለው..ባለማሰብ ውስጥ።

ላለማሰብ አስባለው..ለማሰብ አስባለው። ላለማሰብ ማሰብ ለማሰብ ከማሰብ በላይ አስጨናቂ እንደሆነ በእለት ተእለት ኑሮዬ ተለማምጄዋለው።

አልጫ በጨው ይጣፍጣል፣ ቡና በስኳር ይጥማል የህይወት ማጣፈጫ ምንድነው? ህይወት ምን ጠብ ቢደረግባት ነው ስኳርና ጨው እንደገባበት አልጫና ቡና የምትጥመው? ስል አስባለው። በተለይ የተሰራ እየበላ፣ የተሰፋ እየለበሰ፣ እግሩ መሬት ሳይረግጥ በማርቼዲስ እየሄደ ሰላም ያጣውን የሰፈራችንን ባለስልጣን ሳስብ.. በተለይ እንደ ሀገር በሰፋ ግቢ ውስጥ፣ ቤተ መንግስት በሚመስል ቤት ውስጥ፣ የተለያዩ ዘመናዊ መኪናዎችን እየቀያየረ ደስታ የራቀውን ባለጸጋ አጎቴን በየነን ሳይ.. በተለይ ለገነት በቀረበ ተድላ ውስጥ እየኖረ፣ ባየሁት ቁጥር ምራቄን እየዋጥኩ መች ነው እንደሱ የምሆነው የምልለት፣ አንድም ቀን ፊቱ በፈገግታ ሲፈግ ያላየሁትን ጎረቤታችንን ፍሰሀን ሳስብ ህይወት ታመራምረኛለች። ከሁሉ በላይ ላለማሰብ የማስበውን እኔን ሳስበው ህይወት ያሳስበኛል። ላለማሰብ በማሰቤ ውስጥ ከመኖር ጋር ትግል የገጠምኩ ይመስለኛል። ህይወት የሚጀምረው ከማሰብ እንደሆነ አውቃለው። አለማሰብን ማሰብ ግን በመኖር ላይ ሌላ ጣጣ መጨመር ነው እላለው። እኔም ለመኖር ባልጠና ጫንቃዬ ላይ ብዙ እንቶፈንቶ የተሸከምኩ ነኝ። ርካብ በሳተ በህይወት ቼቼ ላይ በሀሳብ አንቀልባ ተይዞ መኖር እንዴት ይቻላል? ይሄም ያልመለስኩት ሌላው ጥያቄዬ ነው።

ህይወት ሙሉ ነገር የላትም። ቀዳዳ እና ጨምዳዳ ናት። ሙሉ ነው ባልከው ነገሯ ላይ ሸራፋ ሆና ታገኛታለህ። እናም እጠይቃለው..‹ህይወት የምትጥመው እንዴትና መቼ ነው? እያልኩ። የህይወት ጣዕም አሜን እያሉ መኖር ይመስለኛል። ለሆነውና ለሚሆነው ተመስጌን እያሉ ማንጋጠጥ። ህይወት አስር ጊዜ መትረን አንድ ጊዜ የምንቆርጣት የማሰብና የማድረግ ቀመር ናትብዬ በማመንኩበት ማግስት ባለማሰቤ ውስጥ ማሰብ ይፈጠራል። እንዲህ የሚል ‹ህይወት መራራ ናት..እንደ እሬት የጎመዘዘች፣ እንደ ሀሞት የመረረች። ስኳር መሆን የማይችሉ የማይቀምሷት..የማይታገሷት። ስኳር መሆን የቻሉ የሚያጣጥሟት›።

ከሀሳብ ለመገላገል እንጠራራለው..አዛጋለሁ። ከሀሳብ ለመገላገል የማደርገው ጥረት ግን መና ነበር.. ወዳልደረስኩበት የሀሳብ ባህር ነው የሚወረውረኝ። ሀሳብ ከጣለኝ እንጦሮጦስ ውስጥ ቧጥጬና ተንፈራግጬ አፈር ልሼ እነሳለው። አዲስ ነገር በሌለባት አለም ላይ አዲስ ለመሆን እሞክራለው። ጥረቴ ሁሉ ከንቱ ነበር..ከማሰብ የራቀውን እኔን አላገኘውም። እናም ወደነበርኩበት ተመልሼ በአዲስ ሀይል ባለማሰብ ውስጥ አስባለው። ‹በህይወት ውስጥ አዲስ ነገር የለም። የሆነው የሚሆነው ነው። እየሆነ ያለው ከዚህ በፊት የሆነው ነው። እየሄድንበት ያለው መንገድ ያለፈው ትውልድ የሄደበት ነው። ወደፊትም የሚመጣው ትውልድ በዚህ መንገድ ላይ ነው የሚሄደው። ለእኛ ተብሎ የተሰራ የተለየ መንገድ የለም። አለም ሁሌም አንድ አይነት ናት። መኖር በራሱ መደጋገም ነው። ከዚህ በኋላ ሰው ሆነው የሚፈጠሩ ነፍሶች ዛሬ እኔና እናንተ የሆንውን መሆን እጣ ፈንታቸው ነው። ሲመጣ አዲስ ይመስለናል እንጂ አለም ለሰው ልጅ አዲስ ነገር የላትም። ያኛው ትውልድ ያለፈበትን እየደገምነው ነው።

መኖር አዲስ ነገር የለውም። አለም ዛሬም ድረስ እየሰጠችን ያለው ለመጀመሪያው ልጇ አዳምና ቤተሰቡ የሰጠችውን ነው። ሰው በራሱ ውስጥ አዲስ ነገርን ካላገኘ በአለም ውስጥ አያገኝም..› እዚህ ሀሳቤ ጋ ቆምኩ..እስከዛሬ የሚያቆም ሀሳብ አልገጠመኝም ነበር። ይሄ በእስካሁን ማሰቤ ውስጥ ያሰብኩት ምርጡ ሀሳቤ ሆኖ ልቤ ተቀመጠ። በተመስጦ አሰብኩት ‹ሰው በራሱ ውስጥ አዲስ ነገር ካላገኘ በአለም ውስጥ አያገኝም› ሀሳቤ ብርቅ ሆኖብኝ ደገምኩት።

እናም አልኩኝ ህይወት አንድ አይነት ናት..በተደገመና በተደጋገመ፣ በሚደጋገምም ህይወት ውስጥ ነን። አዲስ ነገር በሌላት አለም ውስጥ በመከራዋ ለምን አጽናኝ እስካጣ አለቅሳለው? ደስታዋንስ ለምን የማያልቅ አደርገዋለው? እያልኩ አሰብኩ። ማሰብን መርታት አቅቶኝ ባለማሰቤ ውስጥ ብዙ አሰብኩ።

ሞትን መግደያ..ሀዘንን ማብረጃ ጥበብ አለን። ብርጭቆና ስኒ ውስጥ ጨምረን እንደምናሟሟው ስኳርና ጨው ህይወት እንድትጥመን ማድረግ የእኛ ፈንታ ነው። ፍቅር የህይወት ጨው ነው። የነፍስ ስኳር ነው። መራራውን እንዳጣፈጥንበት አልጫና ቡና መኖርን የምናጣብጥበት። ፍቅር የሰውነት እጣን ነው..የመኖር ጠጅ ሳር ነው። የአለምን ግማትና ጥንባት የምንሸርበት መጽናኛችን።

እንዲህ ያለኝ ህሊናዬ ወዲያው ያድፍብኛል። ፍቅርን አለቃ ብሎ የተቀበለ ሀሳቤ አፍታ ቆይቶ ያብልብኛል። ‹አዲስ ነገር በሌላት አለም ላይ ፍቅርን የህይወት አዲስ ነገር አድርጌ አልቀበልም› ሲል ይሞግተኛል። በሀሳቤ እሸነፋለው..ለሀሳቤ እጅ ሰጥቼ እኔም እንዲህ ማለት እጀምራለው ‹ሀሳቤ ሆይ ልክ ነህ..በአሮጌ አለም ውስጥ ፍቅር አዲስ ሊሆን አይችልም› ስል ሀሳቤ ይሰማኝ ይመስል ድምጼን ከፍ አድርጌ እናገራለው። በራስ ላይ ማመጽ ይሄ አይደል?

ወዲያው ከምስቅልቅል ሀሳቦቼ መሀል ‹ግን እኮ ፍቅር አሮጌ ሆኖ አያውቅም። የሚል ድምጽ ይሰማኛል። የቱን እንደማምን በገዛ ሀሳቦቼ ግራ እጋባለው። የሀሳቦቼ ፈጣሪ እኔው ሆኜ እንደ ፈለጉ የሚያደርጉኝ ግን እነሱ ናቸው። ወደመጀመሪያው ሀሳቤ አደላው..ፍቅርን አሮጌ ብሎ ወደታበየውና ወደተመጻደቀው ሀሳቤ። ሀሳቤን ሳስበው ልክ ነው..እቅል አስቶ በደስታ የሚያሰክርን ፍቅር የነፍስ ጣዕም አድርጌ መቀበል አልተቻለኝም። ለምን ላለኝ እንዲህ የሚል መልስ አለኝ..‹ያፈቀረን እያለ የማያፈቅረንን እየተከተልን፣ የሚወደን እያለ ለሚጠሉን እያጎበደድን ፍቅርን የህይወት ራስ አድርጎ መቀበል አቃተኝ።

ተስፋን ፈራሁት..ፍቅር በሌለበት ልብና ህይወት ውስጥ ተስፋን የሙጥኝ ማለቴ ሞኝነት መሰለኝ። ‹ለምን ሰው ሆንኩ? ከሆንኩኝስ በኋላ ስኳር መሆን ለምን አቃተኝ? ራሴን ጠየኩ..። ምንም እንደማላመጣ ሳይገባኝ ያለስራው ራሴን ኮነንኩት።

ህይወት አሮጌ ከሆነች፣ መኖር ድግግሞሽ ከሆነ፣ አለም አዲስ ነገር ከሌላት፣ ፍቅር ከእስራታችን ነጻ ካላወጣን መኖር ምንድነው? ህይወት ምንድነው? ሰው መሆን ምንድነው? አልኩ። ለነዚህ ሁሉ መልስ አልባ ጥያቄዬ አእምሮዬ ያቀበለኝ አንድ ነገር ብቻ ነበር..መኖር ባይኖር ሲል። ሀሳቤን ተከትዬ እኔም መኖር ባይኖር አልኩ። መኖር ባይኖር እኚህ ሁሉ ውጣ ውረዶች በማን ላይ ይስተናገዱ ነበር? በማን ላይ ነፍስ ይዘሩ ነበር? ማንን ያስለቅሱ፣ ማንን ያሳዝኑ ነበር? ስል ግራ በገባችኝ ህይወት ላይ አምባ ገነን ሆንኩባት። አፍታ አልቆየሁም ሀሳቤ ከዳኝ..‹መኖር ባይኖር እኮ ምንም ነበርኩ። መኖር ስላለ ነው ባለማሰብ ውስጥ አሳቢ የሆንከው›። ሲል የገዛ ሀሳቤ አብጠለጠለኝ።

ባለማሰብ ውስጥ ያሰብኩት፣ በማሰብ ውስጥ የተረዳሁት፣ በማየትና በመስማት በመኖርም የተገነዘብኩት ህይወትና አለም፣ ፍቅርና መኖር ጣዕሙ ካልገባኝ አለመኖር በስንት ጣሙ ልል ከጀለኝ። ግን አላልኩም ሞጋች ሀሳብ አለኝና። ውሸት መሆኔን ሳስብ ፈራሁ። ያሰብኩት፣ የኖርኩት ዘመን ሀሰት መሆኑ ሲገባኝ መኖር አሰጋኝ። ማሰቤ፣ ባለማሰብ ውስጥ ማሰቤ፣ ራሱ ሀሳቤ አሁን ላለው እኔ ምን ፈየደልኝ? ይሄ ሁሉ ካልሆነ ህይወት መዳረሻዋ የት ነው? ከየት ተጀምራ የት ነው ያቆመችው? አላውቀውም። የህግ ፍጻሜ በሆነው ፍቅር ውስጥ ህይወት ሙሉዕነት ከሌለው፣ ጥማ ካላገኘኋት፣ እምነትና እውነት፣ ተስፋና ጽናት ከተፍረከረኩ መኖር ቅሉ ምንድነው?

# ዓለም አቀፍ

## ሥራ አስኪያጁ በሠራተኞቹ ላይ በከፈተው ተኩስ ስድስት ሰዎች ተገደሉ

በአሜሪካ ቨርጂኒያ ግዛት በሚገኘው ዎልማርት ሱፐርማርኬት ለረጅም ጊዜ ያገለገለ ሥራ አስኪያጅ በሠራተኞች ላይ በከፈተው ተኩስ ስድስት ሰዎችን ሲገድል ሌሎች ስድስት ሰዎች  አቆሰለ። በቼሳፒክ በሚገኘው እና ሥራ ወደ ሚበዛበት የሱፐርማርኬቱ ቅርንጫፍ ፖሊስ የተጠራው ግለሰቡ በሠራተኞች ክፍል ውስጥ በባልደረቦቹ ላይ ተኩስ ከከፈተ በኋላ ነበር። ከዚያም መሣሪያውን ወደራሱ አዙሮ በመተኮሱ ባጋጠመው ጉዳት ሕይወቱ ሊያልፍ እንደቻለ ባለሥልጣናት ተናግረዋል።

ሥራ አስኪያጁ ባልደረቦቹን ተኩሶ የገደለበት ምክንያት ምን እንደሆነ እስካሁን ግልጽ አይደለም። ፖሊስም ከግድያው ጋር በተያያዘ እየፈለገ ያለው አካል የለም። ግድያውን የፈፀመው ግለሰብ የ31 ዓመት እድሜ ያለው አንድሪ ቢንግ እንደሚባል ፖሊስ ይፋ አድርጓል። ፖሊስ እንዳለው ግለሰቡ በርካታ ጥይቶች እና ሽጉጥ ታጥቆ ነበር።


ዎልማርት በበኩሉ ከአውሮፓውያኑ 2010 ጀምሮ በድርጅቱ የተቀጠረው ይህ ግለሰብ የማታ ተረኛ እንደነበር ገልጾ፤ “የተጎዱ ሠራተኞቻችንን እና ቤተቦቻቸውን ለማገዝ የምንችለውን ለማድረግ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው” ብሏል። ከሥራ አስኪያጃቸው በተከፈተባቸው ተኩስ ጉዳት ካጋጠማቸው ስድስት ሰዎች መካከል ሁለቱ በአስጊ ሁኔታ ላይ ሲሆኑ፤ አንደኛው ደግሞ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ተገልጿል።

ለፖሊስ የመጀመሪያ ጥሪ የደረሰው ማክሰኞ ምሽት 4 ሰዓት አካባቢ ሲሆን፤ በሁለት ደቂቃ ውስጥ ነበር ወደ ሱፐርማርኬቱ የደረሰው። ከዚያም ወደ ውስጥ በመግባት ሱፐርማርኬቱ ውስጥ የነበሩ 50 ሰዎች እና የተጎዱ ሰዎች እንዲወጡ ካደረገ ከአንድ ሰዓት በኋላ አካባቢው ሰላም መሆኑን ተናግረዋል።

የፖሊስ ኃላፊው ማርክ ሶሌስኪ ረቡዕ ዕለት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ የጥቃቱን ምክንያት ለማጥራት በርካታ ቀናት ሊወስድ እንደሚችል ገልጸው፤ ከፌደራል ፖሊስ (ኤፍቢአይ) ጋር በመሆን ምርመራ እየተካሄደ ነው ብለዋል። የዎልማርትን የደንብ ልብስ የለበሰ አንድ የዐይን እማኝ፣ የሠራተኛው ክፍሉን ለቆ እንደወጣና ተኩስ ከመከፈቱ በፊት ሌላ የሥራ ባልደረባው እንደገባ ተናግሯል።

የዎልማርት ሠራተኛ የሆነው ብሪያና ታይለር ለኤቢሲ ጉድሞርኒንግ አሜሪካ ፕሮግራም ሲናገር “ ሥራ አስኪያጃችን በሩን ከፍቶ ከገባ በኋላ ተኩስ ከፍቷል” ብሏል። ጄሴ ዊልዘውስኪ በበኩሏ ተኩሱ ሲከፈት ጠረጴዛ ሥር ገብታ እንደተደበቀች ተናግራለች።

አንድ ሌላ የዎልማርት ሠራተኛም ሥራ አስኪያጁ ሽጉጡን ከደገነባት በኋላ ወደ ቤቷ እንድትሄድ እንደነገራት አስረድታለች። በርካታ ሠራተኞች




ሥራ አስኪያጁ ቀደም ብሎ ሌሎች ሰዎች አይወዱኝም የሚል ጭንቀት እንደነበረበት እና ስጋታቸውንም ለመንግሥት እንዳሳወቁ ለሲኤንኤን ተናግረዋል።

ፖሊስ ረቡዕ ዕለት በሰጠው መግለጫ፣ ሟቾቹ ሎሬንዞ ጋምብል፣ ብሪያን ፔንድልተን፣ ኬሌ ፓይል፣ ራንዳል ብሌቪንስ እና ትይኔካ ጆንሰን እንደሚባሉ አሳውቋል። ሌላ የ16 ዓመት ታዳጊ በጥቃቱ የተገደለ ሲሆን፣ ታዳጊ በመሆኑ ፖሊስ ስሙን ይፋ አላደረገም።

ሪፐብሊካኑ የቨርጂኒያ ገዢ ግሌን ዮአንኪን፣ ሐዘንን ለመግለጽ ሰንደቅ ዓላማ ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ አዘዋል። “በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት እና ሁኔታውን ለመረዳት ጊዜ ይኖረናል። ዛሬ ግን ያላሰቡትና ያልገመቱት የደረሰባቸው የተጎጂ ቤተሰቦችን የምናጽናናበት ነው” ብለዋል።

ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በበኩላቸው ጥቃቱን “ትርጉም የሌለው እና ዘግናኝ ጥቃት” ብለውታል።“ወሳኝ የሆነ የጦር መሣሪያ ሕግ ማሻሻያን ፈርሜያለሁ። ግን ይህም በቂ አልሆነም” ሲሉ ጨምረው ተናግረዋል። ይህ ግድያ የተሰማው በአሜሪካዋ ግዛት ኮሎራዶ በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን የምሽት ክለብ ውስጥ አንድ የጦር መሣሪያ የታጠቀ ግለሰብ ተኩስ ከፍቶ 5 ሰዎች መገደላቸው እና 17 ሰዎች መቁሰላቸው ከተሰማ ከቀናት በኋላ ነው።

በዎልማርት ሱፐርማርኬትም ተኩስ ሲከፈት ይህ የመጀመሪያው አይደለም። እንደ አውሮፓውያኑ 2019  በቴክሳስ ኤል ፓሶ በሚገኘው ዎልማርት 23 ሰዎች ተገድለዋል። ይህን ግድያ ፈፅሟል የተባለው ግለሰብ ፍርዱን እየተጠባበቀ መሆኑን የዘገበው ቢቢሲ ነው።



## በአፍጋኒስታን ሦስት ሴቶችን ጨምሮ ሕዝብ በተሰበሰበበት ስታዲየም በግርፋት ተቀጡ


በአፍጋኒስታን ሦስት ሴቶችን ጨምሮ 12 ሰዎች በእግር ኳስ ስታዲየም ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በተሰበሰቡበት በግርፋት ተቀጥተዋል። በግርፋት የተቀጡት ሰዎች ዝሙት፣ ሌብነት እና የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት መፈጸምን ጨምሮ ሌሎች “ሥነ ምግባርን የሚጥሱ ወንጀሎች” ላይ በመሳተፋቸው እንደሆነ የታሊባን ባለሥልጣናት ለቢቢሲ ተናግረዋል።

እስላማዊ መሠረት ያለው ታሊባን መሰል ቅጣቶችን ሲፈጽም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ነው።ይህ የታሊባን እርምጃ እንደ አውሮፓውያኑ በ1990ዎቹ ሲተገብራቸው ወደነበራቸው ጠንካራ ቅጣቶች ዳግም እየተመለሰ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው ተብሏል።

ግርፋቱ በተፈጸመባት በምሥራቃዊ የአፍጋኒስታን ክፍል የምትገኘው የሎጋር ግዛት ባለው የታሊባን አስተዳደር ቃል አቀባይ የሆኑት ኦማር ማንሱር ሙጃሂዲ ከቅጣቱ በኋላ ሦስቱ ሴቶች መለቀቃቸውን ገልጸዋል። ቅጣቱ ከተፈጸመባቸው ወንዶች መካከል የተወሰኑት ደግሞ ወደ እስር ቤት መግባታቸውን ተናግረዋል። ወደ እስር የተመለሱት ምን ያህሉ እንደሆኑ ግን አልተጠቀሰም።

ቅጣቱን የተቀበሉት ሰዎች ከ21 እስከ 39 ጊዜ ለሚሆን ጊዜ የተገረፉ ሲሆን፣ ሌላ የታሊባን ባለሥልጣን ከፍተኛው የግርፋት መጠን 39 እንደሆነ መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት



## የአፋር ክልል ስፖርት አዲስ ምእራፍ

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ ታዋቂ በሆነችበት የአትሌቲክስ ስፖርት ስኬት የተመዘገበባቸው ጥቂት ርቀቶች ብቻ ናቸው። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በረጅም ርቀት በርካታ ስመ ጥር አትሌቶችን ካፈሩ አካባቢዎች ባሻገር የአጭር ርቀት አትሌቲክስ እና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ስኬታማ የመሆን እድል እንዳላትም ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይ ከአየር ሁኔታው፣ ከቦታ አቀማመጡ እንዲሁም ከማህበራዊ አኗኗር ጋር ተያይዞ ያልተሰራባቸው ዕምቅ አቅሞች እንዳሉ ይታመናል።

በዚህ ረገድ ትኩረት ካልተሰጣቸው አካባቢዎች መካከል አንዱ የአፋር ክልል ነው፡፡ ይህ ክልል እንደሌሎቹ ሁሉ በተለያዩ ስፖርቶች ፕሮጀክቶችን መስርቶ ለማንቀሳቀስ ሙከራ ቢደረግም ውጤታማ አልነበረም፡፡ በቅርቡ በአካባቢው በነበረው የጸጥታ ሁኔታ ደግሞ የነበሩት ጥቂት ፕሮጀክቶችም መፍረስ እጣ ፋንታቸው ሆኗል። ክልሉ በስፖርቱ ውጤታማ ላለመሆኑ እንደ ምክንያት የሚነሳው በሳይንሳዊ ጥናት የተደገፈና የክልሉ አቅም በየትኛው ስፖርት ላይ ነው በሚል ጥናት ላይ የተመሰረተ ስላልነበረ ነው፡፡ አሁን ግን ክልሉ ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ሳይንስ ምሁራን ጋር በመሆን ባካሄደው ጥናት በተለይ በአጭር ርቀት አትሌቲክስ እንዲሁም በእግር ኳስ ስፖርቶች ላይ ክለብ በማቋቋም በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የአፋር ክልል የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ኡመር ኢብራሂም፤ በክልሉ የነበረው የአትሌቲክስ እንቅስቃሴ ውስን እንደነበረ ያስታውሳሉ፡፡ በክልሉ የነበረው ፕሮጀክትም በሃገሪቷ ተከስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት ፈርሷል፤ ክለቦችም የሉትም፡፡ አሁን ግን ክልሉ የሚጠራበትን ክለብ ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ



**የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የአፋር ክልል ስፖርትን ወደ አዲስ ምእራፍ ለማሸጋገር የተለያዩ ጥናቶችን እየሰራ ነው፣**

ጋር በጋራ በማቋቋም ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ይህንንም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የቴክኒክ ባለሙያዎችም የተመለከቱት ሲሆን፤ ለምስረታው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እና መሰረተ ልማቶች ተዘጋጅተዋል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በብዛት የሚወከለው በረጃጅም ርቀቶች ነው፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህም ይህ ሁኔታ እየቀነሰ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፌዴሬሽኑን «የአትሌቲክስ» እንደማያሰኘውና ስሙን ሙሉ ለማድረግ አጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራትን አካታች መሆን እንደሚገባው ኃላፊው ይገልጻሉ፡፡ በእነዚህ ስፖርቶች ላይ ውጤታማ ለመሆን ደግሞ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ተደራሽ ማድረግ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ከአየር ንብረቱ ባሻገር የህዝቡ አኗኗር አብዛኛውን ጊዜ ለሩጫ፣ ዝላይና ውርወራ ስፖርቶች ምቹ እንደሆነ ይታመናል። በሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና ሌሎች አካላት በተደረገ ጥናትም በእነዚህ ስፖርቶች የተሻለ ስኬት ሊመነዘገብ እንደሚችል ተጠቁሟል። በመሆኑም ይህ ከግምት ገብቶ እና በሳይንሳዊ ዘዴ ታግዞ ኢትዮጵያ በሁሉም የአትሌቲክስ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድትወከል ማድረግ እንደሚያስፈልግ ኃላፊው ተናግረዋል።

አቶ ተመስገን አስናቀ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍል ኃላፊ እንዲሁም የእግር ኳስ ክለቡ ቡድን መሪ ናቸው፡፡ በአፋር ክልል ከዚህ ቀደም ከዳባ የሚባል የእግር ኳስ ቡድን ቢኖርም አሁን ግን መፍረሱን ያስታውሳሉ፡፡ ዩኒቨርሲቲው በ2014ዓም ወጣቶችን ወደ ስፖርት የመመለስ ፕሮግራም መቅረጹን ተከትሎ የክለብ ምስረታው ይሁንታን ለማግኘት ቻለ፡፡ ክለቡ ከተመሰረተ በኋላም አምና ሃዋሳ ላይ በተካሄደው የክልል ክለቦች ቻምፒዮና ሁለተኛ ቡድኑን በማሳተፍ በተያዘው ዓመት ደግሞ በብሄራዊ ሊግ ለመካፈል ምዝገባውን አጠናቋል፡፡

ይህ ፕሮግራም የተቀረጸበት ዋነኛ ምክንያትም ክልሉ ከሌሎች አንጻር በስፖርት ያነሰ ተሳትፎ ያለው በመሆኑ ዘርፉን ለማነቃቃት እንዲሁም በፕሮጀክት የታቀፉ ታዳጊዎችን የሚቀበልና ራዕይ የሚሆናቸው ክለብ በማስፈለጉ ነው፡፡ በቅርቡ ደግሞ ከእግር ኳሱ ጎን ለጎን በአትሌቲክስ (ከረጅም ርቀት ውጪ) እና በውሃ ስፖርቶች ክለቦች የሚቋቋሙ እንደሚሆንም አቶ ተመስገን ይገልጻሉ፡፡ በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች በተደረገ ሳይንሳዊ ምርምር በክልሉ የሚዘወተሩ የባህል ስፖርቶች ፈጣን እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረቱ እንደመሆናቸው በአጭር ርቀት ሩጫ ክልሉ ውጤታማ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው፡፡ ከውሃ ዋና ጋር ተያይዞም የአዋሽ ወንዝ አካባቢ ያሉ ወጣቶችን የተለያዩ ቴክኒኮችን በማሰልጠን ብቻ ተወዳዳሪ ማድረግ እንደሚቻል ያላቸውን እምነት ተናግረዋል።

ከክለቦቹ ምስረታ ጎን ለጎንም በስፖርት መሰረተ ልማት ላይ አስቀድሞ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል። በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው በስፖርት አካዳሚ ደረጃ ጂምናዚየም እና የውሃ ገንዳ ለማስገንባት አቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም በታቀደው ልክ በተጠቀሱት ስፖርቶች ውጤታማ መሆን ሲቻል፤ በቀጣዩ ዓመት (2016ዓ.ም) ደግሞ ክልሉም የራሱ የሆነ ሌላ ክለብ ይመሰርታል በሚል እንደሚጠበቅ አቶ ተመስገን ጠቁመዋል፡፡


## የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ
## ለሸበሌ ባንክ አ.ማ. ባለአክስዮኖች በሙሉ

የሸበሌ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች አንደኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ታህሳስ 9 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ በጅግጂጋ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ሮያል ኢንተርናሽናል ሆቴል ውስጥ ስለሚካሄድ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፤ ሰዓት እና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች፡

1. ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየምና ማጽደቅ፣
2. ምዕላተ ጉባዔውን ማረጋገጥ፣
3. የስብሰባ አጀንዳውን ማፅደቅ፣
4. አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና ነባር አክሲዮኖችን ግዥና ዝውውሮችን መወሰን፤
5. የ2014 ዓ.ም ዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ፤
6. የ2014 ዓ.ም ውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ፤
7. የ2014 ዓ.ም የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተወያይቶ መወሰን፤
8. የጉባዔውን ቃለ ጉባዔ ማፅደቅ፤

**ማሳሰቢያ፡**

- በጉባኤው ላይ በግንባር መገኘት የማይችሉ ከሆነ ጅግጂጋ ከተማ፤ ብሉ ሞል፤ 1 ፎቅ ላይ በሚገኘው የሸበሌ ባንክ ዋና መስሪያ ቤት በመቅረብ የውክልና ቅፅ በመሙላት ከስብሰባው ከሶስት ቀን በፊት ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡
- በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት ቀርባችሁ ውክልና የምትሰጡም ሆነ በጉባኤው በአካል የምትገኙ ባለአክስዮኖች ማንነታችሁን እና ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆናችሁን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ፤ በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ ህጋዊ ውክልና ይዛችሁ ለምትቀርቡ ተወካዮች የወካያችሁን ማንነት የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም ባለአክሲዮን የሆኑ ተቋማት ተወካዮች ተቋማቱን ለመወከል የሚያስችል ሥልጣንና ውክልና የተሰጣችሁ መሆኑን የሚያረጋግጥ ህጋዊ ማስረጃዎችን ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን፡፡
- በውል አዋዋይ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ የያዘ ተወካይ ዋና ማስረጃውን እና ኮፒውን ይዞ በመቅረብበስብሰባው ላይ መሳተፍ ይችላል፡፡

## የዳይሬክተሮች ቦርድ
## ሸበሌ .ባንክ አ.ማ.



ethio telecom

**INVITATION TO INTERNATIONAL COMPETITIVE BID**
**FLOATING DATE: AS OF NOVEMBER 29, 2022**
**RFQ NO. 4231835 & 4231836**

1. Ethio telecom intends to sign a Master Frame Agreement (MFA) contract for one (1) year with a possibility of extension up to a maximum of 3 years with the finally awarded bidder(s). Hence, we are pleased to invite all interested and eligible bidders by this Open International Competitive Bid (ICB) for the Procurement of Fiber optic cable sheath striper and Fiber Identifier with RFQ No. 4231835 and 4231836 respectively. The Tender remains floating from November 29, 2022, to December 22, 2022.

| S. No | Description of Items | Order Qty | U0M | Bid security amount (Birr) | RFQ No. |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Fiber optic cable sheath striper | 162 | Pcs | 15,000.00 | 4231835 |
| 2 | Fiber Identifier | 162 | Pcs | 15,000.00 | 4231836 |

Bid documents can be obtained from Ethio telecom's web sites www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com upon payment of a non-refundable fee of Birr 100.00 (Birr One hundred only) by using tele birr payment platform.

In addition, If you are interested to be on the supplier list of Ethio telecom please register using the following link or copy and paste the link on a browser "https://erp.ethiotelecom.et/OA HTML/jsp/pos/suppreg/Supplier Register. jsp?ouid=0EED8A04B857259C"

2. Interested eligible bidders may obtain further information from ethio's website (i.e. https://www.ethiotelecom.et/tender/ www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com

a. Sealed bids marked as: "Tender for the Supply of Fiber optic cable sheath striper and Fiber Identifier with RFQ No. 4231835 and 4231836 respectively and be addressed to:

**Ethio telecom,**
**Head Quarter**
**Supply Chain Division**
**2nd Floor, Room No.211B,**
**P. O. Box 1047,**
**Addis Ababa, Ethiopia**

b. Bid proposal will be received at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No. 211B, Before or on December 22, 2022 5:00 P.M. Bids presented by any bidder after the closing date shall not be accepted.

3. Bids received in time and fulfilling the other formalities shall be opened in the presence of interested bidders or their legal representatives on December 23, 2022, at 10:00 A.M, at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No.210.

4. Ethio telecom reserves the right to reject all or parts of this bid.

**Ethio telecom**